# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 84ኛ ዓመት ቁጥር 098 ታኅሣሥ 8 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





## ምክክሩ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት መፍትሔ የሚፈለግበት ታሪካዊ መድረክ ነው

- ከኦሮሚያ ክልል በዋናው ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ የሚሳተፉ 320 የሚሆኑ ተወካዮች ይመረጣሉ

መዓዛ ማሞ

አዳማ፡- ሀገራዊ ምክክሩ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት መፍትሔ የሚፈለግበት ታሪካዊ መድረክ ነው ሲሉ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ገለጹ፡፡ ከኦሮሚያ ክልል በዋናው ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ የሚሳተፉ 320 የሚሆኑ ተወካዮች እንደሚመረጡ ተጠቁሟል።

የሀገራዊ ምክክር የኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ትናንት የኦሮሚያ ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ በይፋ ሲጀመር ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንደገለጹት፤ ምክክሩ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሠላም ለማስፈን ዓላማ ያደረገ ነው፡፡ ለግጭትና ለንትርክ የሚዳርጉንን ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት መፍትሔ የሚፈለግበት ታሪካዊ መድረክ ነው፡፡

በኢትዮጵያ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ በሀሳብ መሪዎች እና በፖለቲካ መሪዎች መካከል የሚስተዋሉት አለመግባባቶች እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥኑ መሆናቸውን ጠቁመው፤ እስካሁን ችግሮቹን ለመፍታት የተሄደባቸው መንገዶች ዘላቂ መፍትሔ ባለማምጣታቸው ሀገርንና ሕዝብን ለከፋ ጉዳት እየዳረጉ መሆኑን ተናግረዋል።

ምክክሩ ችግሮችን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ቸን ሃይ

## ቻይና አረንጓዴ ኢኮኖሚያዊ እድገት ለመገንባት በሚደረገው ጥረት በንቃት እየተሳተፈች ነው

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- ቻይና በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ ቀጣይነት ያለው የአረንጓዴ ልማት ለመገንባት በሚደረገው ጥረት በንቃት እየተሳተፈችና ድጋፍ እያደረገች መሆኑን በኢትዮጵያ የቻይና አምባሳደር ቸን ሃይ ገለጹ።

አምባሳደሩ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳሉት፤ ቻይና እኤአ በ2030 የካርቦን ልቀትን ለመቀነስና በ2060 ካርቦን ነፃ የሆነ ኢኮኖሚ ለመገንባት የተለያዩ ስትራቴጂዎችንና ፖሊሲዎችን ቀርጻ በመተግበር ላይ ትገኛለች። በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ ደረጃ ቀጣይነት ያለው አረንጓዴ ኢኮኖሚያዊ እድገት ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ውስጥም በንቃት እየተሳተፈችና ድጋፍ እያደረገች ነው ብለዋል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተነደፈው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብርም በፕሬዚዳንት ዢ ጂንፒንግ ይፋ ከተደረገው ሥርዓት ምሕዳርን የጠበቀ እድገት ማስመዝገብ

ቻይና አረንጓዴ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ፈርጀ ብዙው የተኪ ምርቶች ፋይዳ

መዓዛ ማሞ

### ዜና ትንታኔ

ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ፣ በጨርቃጨርቅና በሌሎች የኢንዱስትሪዎች ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት ላይ በማተኮር መሥራት ከጀመረች ጥቂት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ኢትዮጵያ 2016 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ማድረግ በጀመረችው የተኪ ምርት (import substitute) ስትራቴጂ መሠረት 96 ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት ማቀዷ ይታወቃል። በዚሁ መሠረትም ባለፈው ዓመት ሁለት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ዶላር ያህል የሚያወጡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች መተካት መቻሉን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል፡፡

ምርቶች በዋናነት የምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ውጤቶች ከፍተኛውን ድርሻ (80 በመቶ) የሚይዙ ሲሆን በዋናነት የምግብ ዘይት፣ ፓስታና አልሚ ምግቦች፣ እንዲሁም የቢራ ብቅል ይጠቀሳሉ፡፡ እንደ ሀገር የተጀመረው “የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ” ምርታማነትን ለመጨመር እና ተኪ ምርቶችን ለማሳደግ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ ማዳን የተቻለው የውጭ ምንዛሪ አመላካች ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ምርቶችን ከውጭ ለማስገባት ይወጣ የነበረውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እያስቀሩ መሆኑንም ምሑራት ይናገራሉ፡፡



ተኪ የወጪ ንግድ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት ዘላቂ ኢኮኖሚን ለመገንባት ምን ፋይዳ አለው? የትኞቹ ተኪ ምርቶች ላይስ ማተኮር ያስፈልጋል? እና በመሰል ጉዳዮች ላይ የምጣኔ ሀብት ምሑራንን አነጋግረን ምላሽ ይዘናል፡፡

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገበያ አስተዳደር መምህርና ተመራማሪ የሆኑት ብርሃኑ ቡርጂ (ፕሮፌሰር) ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ የማምረት ፋይዳን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሲገልጹ፤ ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት ሀገሪቷ በውጭ ምርት ጥገኛ እንዳትሆን ያደርጋል ይላሉ፡፡

ፈርጀ ብዙው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በሃይማኖቶች የተወገዘው ሙስና ለምን ፈተና ሆነ?

ገጽ 3




# አሳሳቢው ፆታዊ ጥቃት

**ቤዛ እሸቱ**

**ዜና ሐተታ**



በዓለም ላይ ከሦስት ሴቶች አንዷ ለፆታዊ ጥቃት ተጋላጭ መሆኗን የዓለም ጤና ድርጅት መረጃ ያሳያል። በዓለማችን ላይ ከ15 እስከ 49 የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙና የፍቅር ግንኙነት ውስጥ ከሆኑ ሴቶች መሐል 27 በመቶ በአጋራቸው ፆታዊ ጥቃት እንደደረሰባቸው ይኸው መረጃ ያመለክታል። በሀገራችንም ሁኔታው ተመሳሳይ ሲሆን ባስ ሲልም በቅርብ ቤተሰብ የሚፈጸም ፆታዊ ጥቃትን መሸፋፈን ይታያል።

የኒው ብራይት ኮሙኒቲ ዴቨሎፕመንት ሴንተር ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ፀዳለ ክንፉ፤ ከቀናት በፊት በትዳር አጋሯ ጥቃት የደረሰባት የልጆች እናት አግኝታ ነበር። ባልየው በሚስቱ ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት ሲያደርስ የቆየ ሲሆን በእለቱም የቅርቧ ሰዎች “ለልጆችሽ ብለሽ አይደል እስከዛሬ የቻልሽው አሁንም ለልጆችሽ ብለሽ ቻይው” ሲሏት እንደነበር በቁጭት ታስታውሳለች።

እንደ ሥራ አስኪያጇ ገለጻ፤ እናት ለልጆቿ መኖር የምትችለው እሷ ስትኖር ነው። እሷ እንድትኖር ደግሞ ከጥቃት መጠበቅ አለባት። በተደጋጋሚ ቻይው እየተባሉ በርካቶች ዘላቂ አካላዊ ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ ሕይወታቸውን አጥተዋል፤ ሞራላቸው ተጎድቷል።

እንደ ወይዘሮ ፀዳለ ማብራሪያ፤ ትዳር ሊቆም የሚችለው አጓጉል ድርጊቶች ሲፈጸሙ ቻይው በማለት፤ አይቶ እንዳላየ በማለፍ፤ ሰምቶ እንዳልሰማ በመሆንና ሁሉንም ሸክም ወደሴቷ በማምጣት አይደለም። ወንዱንም ትዳርህ እንዲቆም፤ ልጆችህ እንዲኖሩ፤ ሀገር እንድትቀጥል ጥቃት አታድርስ፤ ለትዳርህ ብለህ ቻለው፤ ጥቃት እያደረሱ መኖር አይቻልም፤ የሚል ማኅበረሰብ መፈጠር አለበት።

እንደማኅበረሰብ ወንዶች ጥቃት ሲያደርሱ ቻይው እየተባለ በዝምታ መታለፉ ለውጥ እንዳይመጣ አድርጓል። ማኅበረሰቡ ይሄንን ይበቃል! ትክክል አይደለም፤ ማለት ከቻለ ነገሮች ይለወጣሉ ስትል ትገልጻለች።

በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሴቶች መብት ስርጸት ባለሙያ አቶ ሙሉዓለም ጌታ እንደሚናገሩት፤ በሀገራችን አብዛኛው ሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች በቅርብ ቤተሰብ የሚፈጸሙ ናቸው። ከቤተሰብ ውስጥ ጥቃቱ ከአባት ይጀምራል። አባት ልጁን እየደፈረ ያለበት ሁኔታ አለ። ከዛም ወንድም አጎት እያለ ይቀጥላል። እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን አካል ነው ጉዳት እያደረሱ ያሉትና ይህንን አውቀው ከድርጊታቸው መቆጠብ አለባቸው።

እንደ አቶ ሙሉዓለም ማብራሪያ፤ በኅብረተሰቡ ዘንድ በቅርብ ቤተሰብ የሚፈጸም ጥቃት ሲያጋጥም ለተጠቂ ድጋፍ ከመስጠትና ለሕግ አካላት ከማሳወቅ ይልቅ ዞረው ይገናኛሉ በማለት ዝምታን መምረጥ አለ። ፆታዊ ጥቃት የሴትን ሰብዓዊ መብት መጣስ ነውና በማንም ተፈጸመ በማን መፈጸሙን ያወቁ አካላት ለሕግ አካላት ማመልከት አለባቸው። ባልና ሚስት ናቸው ነገ ዞረው ይገናኛሉ በማለት ዝም መባል የለበትም።

ወንጀል ስለሆነ ወንጀሉን ማጋለጥና ለሕግ አካል አሳልፎ መስጠት ይገባል። እነሱ ነገ ተመልሰው ቢገናኙም ድርጊቱ ጥፋት እንደሆነ ማወቅ አለባቸው። ጥቃቱ የደረሰው በትዳር አጋር ከሆነና ተገቢውን ቅጣት አግኝተው ወደ ትዳር የሚመለሱ ከሆነ ጥቃቱ ድጋሚ አይፈጸምም። ተሸፋፍኖ ዝም ሲባል ነገም ሌላ ጥቃት እንዲፈጸም ማበረታታት ነው ሲሉ ያብራራሉ።

የእሸት ችልድረን ኤንድ ዩዝ ዲቨሎፕመንት ኦርጋናይዜሽን ሥራ አስኪያጅና የሜን ኢንጌጅ ኢትዮጵያ ስትሪም ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ሲሳይ ታረቀኝ የሚመሩት ሜን ኢንጌጅ 27 ድርጅቶችን በአባልነት የያዘ ንቅናቄ ሲሆን ፆታዊ ጥቃትን ለመከላከል ወንዶች አጋር መሆን አለባቸው በማለት እንደሚንቀሳቀሱ ይገልጻሉ።

እንደ አቶ ሲሳይ ማብራሪያ፤ የሴቶች ጥቃትን ለመከላከል በሀገራችን የፆታ እኩልነትን ለማምጣት የተሠሩት ሥራዎች በአብዛኛው ሴቶች ላይ ያተኮረና ወንዶችን የዘነጋ ነው። የሜን ኢንጌጅ ንቅናቄ ይሄንን ክፍተት ለመሙላት በማሰብ ወንዶች የሴቶችን መብት እንዲያውቁና እንዲያከብሩ ለማድረግ ያለመ ነው።

በሀገራችን ሴት ልጅ የትዳር አጋሯ ሲደበድባት “ባሏ አይደል ምን ችግር አለው” የሚል ተገቢ ያልሆነ አስተያየት ይሰጣል። ይሄና መሰል አመለካከቶች በግንዛቤ እጥረት የተነሳ በመሆኑ ለመቀየር የግንዛቤ መፍጠር ሥራዎች ያስፈልጋል ይላሉ።

ሆኖም በማኅበረሰቡ ዘንድ ሥር የሰደደ አመለካከት በመሆኑ በአንድ ጀንበር አይቀየርም የሚሉት አቶ ሲሳይ፤ ከለከፋ ጀምሮ ጥቃት መሆኑን ማስረዳት ያስፈልጋል። ለከፋ ጥቃት የማይመስለው ብዙ ሰው እንደሆነ ይናገራሉ። ምንም እንኳን ባሏ ቢሆን፤ ፍቅረኛዋም ቢሆን መብቷንና ፍላጎቷን ማክበር እንዳለበትና በአካሏ የማዘዝ መብት የእሷ መሆኗን ማስረዳት ያስፈልጋል። ለዚህም ከቤተሰብ ጀምሮ፣ በትምህርት ቤት ተማሪዎች እንዲያውቁት ማድረግ ያስፈልጋል ነው ያሉት።

በተለይ ታዳጊዎች ከልጅነታቸው አንስቶ እያወቁት እንዲመጡ ቤተሰብም ሴትና ወንድ ልጅን እኩል የማሳደግ ባሕል ሊያዳብር ይገባል። ይህም በተወሰነ ድርጅትና ግለሰቦች እንቅስቃሴ ሳይሆን በሁሉም ሰው ጥረት የሚመጣ መሆኑን ጠቁመዋል።

የፆታ ጥቃትን በተመለከተ እራሱን የቻለ ሕግ ሊኖር ይገባል ብለን እናምናለን፤ የሚሉት አቶ ሲሳይ፤ ለዚህም የሥርዓተ ፆታ ሕግ ያስፈልጋል ብለዋል። የሴቶችም ሆነ የወንዶች መብትና ግዴታዎች በዝርዝር ሊሰፍሩ ይገባል በሚል የአድቮኬሲ ሥራ እየሠራን ነው ይላሉ።

እንደ አቶ ሙሉዓለም ገለጻ፤ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍትሕ ሚኒስቴር ጋር በመሆን ከሴቶች አንጻር ያሉ ሕጎች ያሉባቸው ክፍተቶች ተለይተዋል። ባሉት ሕጎች ላይ ያልተካተቱና አሁን ላይ የመጡ የወንጀል ተግባራት አሉ። የነበሩትም ተሻሽለው በቀጣይ አስተማሪ የሆነ እርምጃ መውሰድ የሚያስችል የሕግ ማሕቀፍ እንዲዘጋጅ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ እየተሠራበት እንደሆነ ይጠቁማሉ።

እንደ አቶ ሲሳይ ማብራሪያ፤ አዲስ ሕጎችን ከማውጣት ባሻገር ያሉት ሕጎች የአፈጻጸም ችግር አለባቸው። ለረዥም ጊዜ ሲባል የቆየው የአፈጻጸም ክፍተት ከንግግር ባለፈ የማስተካከያ ጊዜው አሁን ነው። አስፈላጊ የሆኑ ግን የሌሉ ሕጎች ሊወጡና ያሉትም ሕጎች በትክክል ሊተገበሩ ይገባል። በፆታዊ ጥቃት ላይ ችግሩ እራስ ላይ እስኪደርስ የመጠበቅ ሁኔታ አለ። የሕግ አካላት ችግሩን እንደራሳቸው በማየት የተፋጠና ፍትሕ እንዲሰጥ መትጋት አለባቸው።

እንደ ወይዘሮ ፀዳለ ገለጻ፤ የሃይማኖት አስተምሕሮዎቻችን ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ እየተተረጎሙ ነው። ሃይማኖታዊ አስተምሕሮዎቻችን ላይ የወንዶችን የበላይነት የሚሰብክ ነገር ባይኖርም ሰዎች እንደሚመቻቸው እየተረጎሙት ነው። የሃይማኖት ተቋማትም ይሄንን በጽኑ መቃወምና ትክክለኛውን ትርጓሜ ማኅበረሰቡ ጋር እንዲደርስ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

# የአሽከርካሪዎችን ቅሬታና የትራፊክ ሕጉን ለማስታረቅ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

**ዜና ሐተታ**

ስሙን ዘነበ አዲስ ሲል ያስተዋወቀኝ አንድ የራይድ አሽከርካሪ ለዓመታት በማሽከርከር ሙያ ላይ ቆይቷል። እንደ እሱ ዕምነት ሁሌም ቢሆን የትራፊክ ሕጎችን አክብሮ በመጓዝ ጠንቃቃ ከሚባሉት ሾፌሮች አንዱ ነው። በዚህ ምክንያትም እስከዛሬ ሕግ ጥሶ ለጥቃት የተዳረገበት አጋጣሚ አልነበረም።

ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ግን በርካታ የትራፊክ ፖሊሶች ያለአንዳች በቂ ምክንያት አሽከርካሪዎችን በማሳደድ በገንዘብ እየቀጡ ነው ይላል። እሱም ቢሆን የችግሩ ሰለባ መሆኑን ይናገራል። ዘነበ በአንድ ወር ከአስራ አምስት ቀናት ብቻ ለስድስት ጊዜ ‹‹ደንብ አላከበርክም›› በሚል በትራፊኮች ተከሶ ተቀጥቷል።

እሱ እንደሚለው የተላለፈበት ቅጣት ፈጽሞ ያልተገባና አስተውሎት የጎደለው ነው። ‹‹ማንም ቢሆን ባጠፋው ልክ መቀጣት እንዳለበት አምናለሁ›› የሚለው ዘነበ፤ ያለአግባብ ጥፋተኛ መባል ግን ከአስተማሪነቱ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል ሲል ተናግሯል ።

ሌላው ስሙ እንዲጠቀስ ያልፈለገ የከባድ መኪና አሽከርካሪም የሰሞኑን የትራፊክ ፖሊሶች ክስና ቅጣት ላይ ቅሬታውን ያሰማል። አሽከርካሪው ለዚህ የሚያነሳው ምክንያት ‹‹አንዳንድ ትራፊኮች ለመቅጣት ሲሉ ይጠቀሙበታል›› የሚለውን ያልተገባ ስልት ነው። እንደ እሱ አስተያየት ትራፊኮች በደንብ ልብሳቸው ቆመው ሕግና ሥርዓት ሲያስከብሩ ማየት ለተመልካች ጭምር ክብርና ትርጉም አለው። አንዳንዶቹ ግን ራሳቸውን ከእይታ ሰውረውና በአሳቻ ቦታ ተደብቀው አሽከርካሪዎችን ለመቅጣት የሚዘጋጁ ናቸው። እንዲህ ማድረጋቸው ለክስና ቅጣት እንዲያመቻቸው ነው የሚለው አሽከርካሪ፤ ማንም ባጠፋው ልክ መቀጣት እንዳለበት ዕምነቱ እንደሆነ ይናገራል።

እንደ ዘነበ ገለጻ፤ አንዳንድ ትራፊክ ፖሊሶች አሽከርካሪዎች በሚቆሙባቸው የተለያዩ ሥፍራዎች ሰበብ እየፈለጉ መቅጣትን ልምድ አድርገውታል። ቅጣቱም በሕክምና ቦታዎች፣ በቅርበት ድጋፍ የሚሹ ደንበኞችን ችግር ሳይቀር ከግምት ያስገባ አይደለም። ይህን በመፍራት መብራት ጥሰው የሚሄዱ፣ በፍጥነት የሚያሽከረክሩ፣ መከሰስን ከልምድ ቆጥረው ራሳቸውን ለቅጣት የሚያዘጋጁ ግዴለሽ አሽከርካሪዎችን አበራክቷል ባይ ናቸው ።

የአሽከርካሪዎችን ቅሬታ በተመለከተ በሰሞኑን በተለያዩ አካባቢዎች ባደረግነው ቅኝት ተመሳሳይ አጋጣሚዎችን አስተውለናል። ትራፊክ ፖሊሶች በርካታ አሽከርካሪዎችን እያስቆሙ ይቀጣሉ፣ ታርጋ ይፈታሉ። በዚህ ዙሪያ ከተለያዩ አሽከርካሪዎች የሚሰማው ሀሳብ ደግሞ በትራፊክ ፖሊሶች ላይ የሚያነጣጥር ቅሬታን የያዘ ነው። አብዛኞቹ ሾፌሮች ‹‹የትራፊክ ፖሊሶች ያለአግባብ ይቀጡናል፣ ያሳቅቁናል››። በሚል ወቀሳ የሚያሰሙ ናቸው። እነሱ ጥቂት የማይባሉ የትራፊክ ፖሊሶች እኛን ከማስተማር፣ ግንዛቤ ከማስጨበጥ ይልቅ መቅጣትን ያስቀድማሉ ብለው ያምናሉ።

በከተማችን አሽከርካሪዎች አጋጥሞናል ለሚሉት የመንገድ ላይ ቅጣት ምላሽ የሰጡት በአዲስ አበባ ፖሊስ ትራፊክ ቁጥጥር መምሪያ የትራፊክ ሙያና ሕዝብ ግንዛቤ ዲቪዠን ኃላፊ ኢንስፔክተር ሰለሞን አዳነ ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፤ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ የትራፊክ ቁጥጥሩ በከፍተኛ ትኩረት እየተሠራ ቢሆንም የአደጋው መጠን ግን ካለፉት ጊዜያት ባነሰ መልኩ እየቀነሰ አይደለም። በየጊዜው ደንብ የሚተላለፉና ሕግ የሚጥሱ አሽከርካሪዎች ተበራክተዋል። ችግሩን ለመታደግ ፖሊስ የግንዛቤ ማስጨበጫ ከመስጠት ባለፈ ጠንካራና ተደራሽ የሚባል የሕግ ማስከበር ሥራን እየተተገበረ ይገኛል።

እንደ ኢንስፔክተር ሰለሞን አገላለጽ፤ ሁሉም የደንብ መተላለፎች የትራፊክ አደጋን ያስከትላሉ። በዘንድሮው



የመጀመሪያው ሩብ ዓመት በነበረው ቁጥጥርም 652 ሺ 445 አሽከርካሪዎች ደንብ በመተላለፋቸው ተቀጥተዋል። ይህ ማለት አሽከርካሪዎቹ እንደሚሉት ሳይሆን የግንዛቤ ማስጨበጫ ያገኙትን በርካቶችን ቁጥር ሳያካትት ነው።

የትራፊክ ፖሊሶች ከቀኑ እንቅስቃሴ ባለፈ ሌሊቱን ጨምሮ 24 ሰዓት ቁጥጥር ያካሂዳሉ ያሉት ኃላፊው፤ ይህም ለትራፊክ አደጋ የተሰጠውን ልዩ ትኩረት የሚጠቁም ነው ብለዋል።

አሽከርካሪዎቹ ደጋግመው ስለሚያነሱት ቅሬታ ምላሽ ሲሰጡም የትራፊክ መምሪያው ዋና ዓላማ በየጊዜው በአደጋ የሚጠፋውን ሕይወትና ንብረት መታደግ እንጂ ገንዘብ መሰብሰብ ላይ ያነጣጠረ አይደለም ሲሉ ተናግረዋል።

በተለያዩ ጊዜያት ቅሬታዎች እንደሚነሱ የሚያምኑት ኃላፊው፤ ለችግሩ መፍትሔ ለመስጠትም ለትራፊኮች የአቅም ግንባታ ሥልጠናና የሥራ መመሪያ በመስጠት የድጋፍና የክትትል ሥራ እንደሚካሄድ ጠቁመዋል። ማንኛውም ጤናማ ጥቆማ ቢደርስ ግን መምሪያው እያረመና እያስተካከለ ለመሄድ ዝግጁ መሆኑን አስታውቀዋል።

የዘንድሮው የትራፊክ ቁጥጥርና የመስክ ምልከታ ግምገማ የመንገድ ላይ የትራፊክ አደጋን የሚያስከትሉ የደንብ ጥሰቶች በስፋት መኖራቸውን አመላካች ሆኗል። አደጋው በከተማችን የሚካሄደውን የኮሪደር ልማት ጭምር ሰለባ ያደረገ ነው፤ ችግሩን በተለየ ትኩረት ለመፍታትም በስፋት እየተሠራበት እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ሙያዊ ኃላፊነታቸውን ጠብቀው የሚያሽከረክሩ እንዳሉ ሁሉ የሕግ ጥሰት በሚፈጽሙት ላይ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ይሆናል የሚሉት ኢንስፔክተር ሰለሞን፤ የቁጥጥር ሥራውን ከዓለም አቀፉ የትራፊክ ሕግ ማሕቀፍ ጋር በማያያዝም በሀገራችን ጠንካራ ሕግ ከጠንካራ የሕግ ማስከበር ጋር በእኩል ሊቀናጅ ግድ እንደሚል ጠቁመዋል።

# የተመጣጠነ ምግብ ተደራሽነት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው

## - በቀድሞው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የተቋቋመው “የአዳም ፋውንዴሽን” ይፋ ሆነ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የተመጣጠነ ምግብ ተደራሽነት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ መሆኑን የቀድሞው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ።

የቀድሞው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን የአዳም ፋውንዴሽን የማብሰሪያ ሥነሥርዓት ትናንት በአዲስ አበባ ሲካሄድ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ ባሳለፍኳቸው የመሪነት ዘመን የተመጣጠነ ምግብ ተደራሽነት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ተረድቻለሁ።

በቀጣይ የተመጣጠነ ምግብ ተደራሽነትን በማስፋፋት ለኢትዮጵያ እና ለአፍሪካ ብልፅግና የድርሻዬን ለመወጣት ቁርጠኛ ነኝ ሲሉ አስታውቀዋል።

የተመጣጠነ ምግብ ለኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ እድገት ሞተር በመሆኑ የተመጣጠነ ምግብ ተደራሽነትን ማሳደግ የግድ መሆኑን አመላክተዋል።

በአፍሪካ ያለውን መቀንጨር በመግታት በአዕምሯዊ እና አካላዊ እድገት የዳበረ የሰው ኃይል ለማፍራት ቅድሚያ የሚሰጠው ሥርዓተ ምግብ ተደራሽነት መሆኑን ገልጸው፤ ለዚህ ደግሞ የሀገራት መሪዎችን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በትብብር እና በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

ሕጻናት የተሟላ ስብዕና እና ጤንነት እንዲኖራቸው ከጽንስ እስከ ሁለት ዓመት ባሉት ጊዜያት የተመጣጠነ ምግብ ለማቅረብ ሰፊ ሥራ ይጠይቃል ነው ያሉት።

የመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት የነገ ትውልድን ለማፍራት የርብርብ ማዕከል ናቸው ያሉት አቶ ደመቀ፤ ለሕጻናት አዕምሯዊ እና አካላዊ እድገት የተመጣጠነ ምግብ ማቅረብ መተኪያ የለውም ሲሉ ተናግረዋል።

ለልጆች ጥሩ ትምህርት ቤት የሚያስፈልገውን ያህል የተመጣጠነ ምግብ ማቅረብም የሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነት መሆኑን አስታውቀዋል።

የተመጣጠነ ምግብ እጥረት በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ጎልቶ እንደሚታይ ገልጸው፤ ችግሩን መፍታት የሚያስችል የአዳም የፋውንዴሽን ተቋቁሟል ነው ያሉት።

ምግብ ማቀነባበር፣ ጤናና ሥርዓተ ምግብን ማሻሻል እንዲሁም ግብርና፣ ትምህርትና ማኅበራዊ ጥበቃ የአዳም ፋውንዴሽን ቅድሚያ የሚሰጣቸው የትኩረት መስኮች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ፋውንዴሽኑ የአጀንዳ 2063 እቅድን ለማሳካት አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ እና ከሀገራዊ የልማት ትሩፋት እና ከምግብ ሥርዓት ንቅናቄዎች ጋር የተቆራኘ መሆኑን አስረድተዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም፣ የተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት መርጃ ድርጅት (ዩኒሴፍ)፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ የጤና እና የግብርና ሚኒስቴር እና ሌሎች በርካታ ተቋማት የፋውዴሽኑ አጋሮች መሆናቸውን አመላክተዋል።

ፋውንዴሽኑ በኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን በቁጥር 7260/24 የተመዘገበ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት መሆኑ ታውቋል።

# በሃይማኖቶች የተወገዘው ሙስና ለምን ፈተና ሆነ?

**ነፃነት ዓለሙ**

ጉቦ ማለት መብትን መግዛት ነው ይላሉ። እንደ ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን እንደ ስብዕናም ነውር መሆኑን ይገልፃሉ። በሃይማኖቱ የደከሙበትን መስጠት እንጂ ያልደከሙበትን መቀበል አይፈቀድም የሚሉት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መምህር የሆኑት መጋቢ ሀዲስ ዓለማየሁ እሸቱ፤ ድርጊቱ ወንጀል፣ ርኩሰት፣ የሕዝብና የሀገር ዕድገት ልጓም መሆኑን ይገልፃሉ።

በሠለጠኑ ሀገራት ሙስና የለም ማለት ባይቻልም የሰውን መብት የሚነኩ፣ የሰውን ጤና የሚያቃውሱና የሰውን የዕለት ተዕለት ኑሮ የሚነኩ ጉዳዮች ላይ ግን ሙስና የለም ይላሉ። ያ የሆነው ደግሞ ሕዝባቸው ሃይማኖተኛ ስለሆነ ሳይሆን ጠንካራ ሕግ በመኖሩ ነው የሚሉት መምህሩ፤ የሃይማኖት አባቶች ብቻ ሳይሆኑ መንግሥትም ሕዝቡን ከዚህ እኩይ ድርጊት መጠበቅ አለበት በማለት ያስረዳሉ።

በሌላ በኩል ሃይማኖቶችስ ይህን እንድንፀየፍ እየነገሩን ነው ወይ?፣ ተሰሚነታቸውስ እስከምን ድረስ ነው፣ የሚናገሩበት ቋንቋ ለሰሚዎቻቸው የሚመጥንና አመለካከታቸውን የሚቀይር ነው ወይ የሚለውን ከእምነት ተቋማት ጋር መነጋገር ያስፈልጋል ይላሉ። መንግሥት ወይም ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽንም ከሃይማኖት ተቋማት ጋር ተገናኝቶ መሥራት እንዳለበት ይጠቁማሉ።

የሞራል ልዕልና ካለመኖሩ አኳያ ጉቦ ተቀባዩ ደረቱን ነፍቶ እየሄደ የሚታይበት ሁኔታዎች እንዳሉ ጠቅሰው፤ መንግሥት ሾፌር ነው ማኅበረሰቡ ተሳፋሪ ነውና መንግሥት ጠበቅ ያለ ሕግ ካወጣና የሃይማኖት ተቋማት ጋር ያለው ትምህርት ከተጠናከረ ማኅበረሰቡ ከዚህ ውጪ ሊሆን አይችልም ነው ያሉት።

የእስልምና ሃይማኖት መሪ የሆኑት ሼህ ሁሴን አወል የግብረገብ ትምህርቶች በትምህርት ማዕከላት አለመሰጠቱ፣ የሃይማኖት አባቶች በጉዳዩ ላይ ትኩረት ሰጥተው አለማስተማራቸው እንዲሁም እንዲህ ያሉ ሰዎች ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ አለመወሰዱ ነው ይላሉ። የእነዚህ ሦስት ነገሮች መላላት ደግሞ ኅብረተሰቡ ድርጊቱን እንዲላመደው አድርጓል የሚሉት የሃይማኖት መሪው፤ ፀያፍ የሆኑ ነገሮች አንድ ተብለው ከተጀመሩ ሁለት ብሎ ለመሄድ በጣም ቀላል ነው ይላሉ።




እንደእስልምና ሃይማኖት አስተምሕሮ ሕዝብን ማገልገል ከፈጣሪው የሚሰጥ ኃላፊነት ነው የሚሉት የሃይማኖት መሪው፤ ጉቦ መስጠትም፤ መቀበልም አስነዋሪ ነው በማለት ያስረዳሉ። ጉቦ ሰጪው ኃላፊነት ላይ የተቀመጠውን ሰው ያሳስተዋል፤ ተቀባዩም ጉቦ ካለ በሚል ፍትሕን የማዛባት ሥራን ይሠራል ይላሉ። የዕድገት ፀር፣ የሠላም ፀር እንዲሁም የፍቅር ፀር ነው በማለት ገልፀው፤ በእስልምና ሃይማኖት የተወገዘ ተግባር መሆኑን ይገልፃሉ።

ሙስናን የሚፀየፍ ትውልድ ለመፍጠር ሕጋዊ አሠራር ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የገለፁት መሪው፤ ማኅበረሰቡ ፈጣሪውን መፍራት እንደሚገባው ይናገራሉ። ጉቦ መስጠትም ሆነ መቀበል የሀገር ኢኮኖሚ እንዲንኮታኮት ያደርጋል፤ ፍቅርን ያጠፋል፤ ስግብግብ ሰዎችን ያበዛል ይላሉ። ከዚህ አኳያም የሚመለከተው ሁሉ ከዚህ ድርጊት ይራቅ ኃላፊነት ላይ ያሉ ሰዎችም ነፍሳቸውን በማሸነፍና ስሜታቸውን በመግዛት ከድርጊቱ እንዲቆጠቡ የሚል መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ከባሕላችን፣ ከሞራል እሴቶቻችንና ከሃይማኖቶቻችን አንፃር እንኳ የድርጊቱን ነውርነት፣ አጸያፊነቱና ጉዳቱ ግልጽ በመሆኑ ከወዲሁ አምርረን ልንታገለው ይገባል ሲሉ ነው የሃይማኖት አባቶች ምክረ ሀሳብ የሰጡት።

# ለኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥና ለአደጋ መንስኤ የሆኑ ችግሮችን የመፍታት ሥራዎች እየተሠሩ ነው

## - ዛፎች ለኃይል መቆራረጥ 47 በመቶ ድርሻ እንዳላቸው በጥናት ታውቋል

**ኢያሱ መሰለ**

አዲስ አበባ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ ለኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥና ለአደጋ መንስኤ የሆኑ ዛፎችን እየቆረጠ መሆኑን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ፤ በኤሌክትሪክ መስመሮች አቅራቢያ ያሉ ዛፎች ለኃይል መቆራረጥ 47 በመቶ ምክንያት እየሆኑ እንዳሉም በጥናት ተለይቷል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮሙዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ መላኩ ታየ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከኤሌክትሪክ መስመሮች ጋር ንክኪ ፈጥረው ለኃይል መቆራረጥና ለተለያዩ አደጋዎች መንስኤ የሚሆኑ ዛፎች እየተቆረጡ ነው። ዛፎች እና ግንባታዎች ከኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ከሦስት ሜትር በላይ ርቀው መገኘት እንዳለባቸው የተቀመጠ መመሪያ እንዳለ ጠቅሰው፤ ይህ መመሪያው በአንዳንድ ቦታዎች ተግባራዊ ባለመሆኑ ዛፎች ቅርንጫፎቻቸው እየተንሰራፋ ለኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥና ለተለያዩ አደጋዎች መንስኤ እንደሆኑ ገልጸዋል።

ችግሩ ከግንዛቤ ማነስና ሕግ ከማስከበር ጉድለት እንደተከሰተ አስረድተው፤ ተቋሙ በአንድ በኩል ሚዲያዎችን በመጠቀም ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች እየሠራ እንዳለና በሌላ በኩል የአደጋ ስጋት የሆኑ ዛፎችን እየቆረጠ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት መስመሮችን ሲዘረጋ በዘፈቀደ ሳይሆን የከተሞችን ማስተር ፕላን ተከትሎ ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ መሠረተ ልማቱ ከተዘረጋ በኋላ የሚሠሩ ግንባታዎች፣ የሚታጠሩ አጥሮች፣ የሚተከሉ ዛፎች ወደ ኤሌክትሪክ መስመሩ ከመጠጋት አልፈው መስመሩ በላያቸው ላይ አቋርጧቸው የሚሄድበት ሁኔታ እንዳለ አስረድተዋል። ይህ ሁኔታ ለኃይል አቅርቦቱ መስተጓጎልና ለአደጋዎች መጨመር ምክንያት እየሆነ መጥቷል ብለዋል።

በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶች ላይ ችግር የሚፈጥሩ ዛፎችን መቁረጥ አሁን የተጀመረ አይደለም ያሉት አቶ መላኩ፤ አሁን በስፋት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈለገው በኃይል መቆራረጥ ላይ የሚፈጥሩት ተፅዕኖው 47 በመቶ በመድረሱ እንደሆነ አስረድተዋል።

ገና ከጅምሩ በተወሰዱ ርምጃዎችም የኃይል መቆራረጥ ድግግሞሽ በእጅጉ መሻሻሉን ተናግረዋል። የበለጠ ቢሠራበት የተሻለ ውጤት እንደሚያመጣ ታምኖበት በመላ ሀገሪቱ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል ነው ያሉት። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኤሌክትሪክ ምሰሶዎችን እና ገመዶችን ተጠግተው የሚፈጸሙ ግንባታዎችም ሥርዓት እንዲይዙ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ስለመሆኑ ጠቅሰዋል።

በአረንጓዴ ዐሻራና በኮሪደር ልማት የሚተከሉ ዛፎችን በተቀመጠው መመሪያ መሠረት ከኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶች አርቆ መትከል እንደሚገባም ተናግረዋል። የኮሪደር ልማት ባለባቸው አካባቢዎች የኤሌክትሪክ መስመሮች በመሬት ስር መተላለፍ መጀመራቸውን እንደ ጥሩ መፍትሔ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሙሉ ለሙሉ እዚህ ደረጃ ላይ እስከሚደርስ ዛፎችን ከኤሌክትሪክ መስመሮችና ምሰሶዎች አርቆ መትከል መረሳት እንደሌለበት ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር በርካታ ዛፎችን እንደተከለ ጠቅሰው፤ ዛፎችን የሚቆርጠው የሚያስከትሉትን ሰብዓዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ለማስቀረት መሆኑን አስረድተዋል።

በዛፍ ቆረጣው ዘመቻ ብዙኃኑ እየተባበረ እንዳለና አንዳንድ ግለሰቦች ግን ለምን ዛፉችን ይቆረጣል በሚል አምባጓሮ እንደሚያነሱ ጠቅሰው፤ የሚመለከታቸው አካላት ተቋሙ የሚሠራውን ሥራ እንዲደግፉና ሕግ የማስከበር ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ አቶ መላኩ ጥሪ አቅርበዋል።

# የመግባቢያ ሰነዱ የንግዱን ዘርፍ ማነቆዎች በመፍታት ሰው ተኮር ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው

**ታደሠ ብናልፈው**




አዲስ አበባ፡- የመግባቢያ ሰነዱ በንግዱ ዘርፍ የሚታዩ ችግሮችን በመፍታት ሰው ተኮር ልማትንና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆኑ ተገለጸ፡፡ መንግሥት ለግሉ ዘርፍ የሚሰጠውን ድጋፍ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተጠየቀ ።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ንግድ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚኖርን ሁሉን አቀፍ የምክክር መድረክ ማጠናከር የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ትናንትና ተፈራርመዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አብዱልሐኪም ሙሉ (ዶ/ር) በሥነ ሥርዓቱ ላይ እንደገለጹት፤ ስምምነቱ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ያለውን ሁሉን አቀፍ ምክክር በማጠናከር እየተሠራ ያለውን ሰው ተኮር ልማትና ኢኮኖሚያዊ እድገትን እውን ለማድረግ የሚረዳ ነው፡፡

ስምምነቱ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚኖርን ሁሉን አቀፍ የምክክር መድረክ ለማጠናከር በንግዱ ዘርፍ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠትና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማስመዝገብ ትልቅ ሚና እንዳለው አመልክተዋል፡፡

መንግሥት ባለፉት ስድስት ዓመታት ለግሉ ዘርፍ ምቹ የሥራ ምሕዳር በመፍጠር፤ ትኩረትና ድጋፍ በማድረግ የሀገሪቱ ኢኮኖሚን እያሳደገ ይገኛል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ኢኮኖሚውን ይበልጥ ለማሳደግና እየተሠራ ያለውን ሰው ተኮር ልማት እውን ለማድረግ መንግሥት ከግሉ ዘርፍ ጋር ያለውን ግንኙነት እያጠናከረ ነው ብለዋል፡፡

የተፈረመው ስምምነት በንግዱ ዘርፍ አካታችነት እንዲስፋፋ፤ ኢንቨስትመንት እንዲነቃቃና ተደራሽነት እንዲስፋፋ ትልቅ አስተዋፅዖ አለው ሲሉም ገልጸዋል። ቀልጣፋና ፈጣን የኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲመዘገብ፤ በንግዱ ዘርፍ እየገጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች በዘላቂነት እንዲፈቱ ለማድረግ፤ ለዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ትልቅ ፋይዳ እንዳለውም አስታውቀዋል፡፡

በንግዱን ዘርፍ እያጋጠሙ ላሉ ተግዳሮቶች ዘላቂ መፍትሔ በመስጠት፤ ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር፤ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች እንዲሻሻሉ በማድረግ፤ ሰው ተኮር ልማትንና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማረጋገጥ እየተሠራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉም ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ በበኩላቸው፤ ስምምነቱ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ያለውን ግንኙነት በማጠናከር እየተሠራ ያለውን ሰው ተኮር ልማትና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማሳለጥ ያግዛል ብለዋል።

መንግሥት የግሉን ዘርፍ የሚያበረታቱና ምቹ የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ የኢኮኖሚ ሕጎችና ፖሊሲዎችን በማሻሻል፣ የተሻሻሉ ሕግና ፖሊሲዎች አፈፃፀማቸውን በመከታተል አስተማማኝ የሆነ ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማምጣት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ስምምነቱ የግሉ ዘርፍ ከመንግሥት ጋር ያለውን የምክክር መድረክ በማጠናከር መንግሥት ለግሉ ዘርፍ ትኩረት እንዲሰጥ፤ የግሉ ዘርፍም በኢኮኖሚው እድገት ያለውን ሚና እንዲወጣ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና እንዳለው አመልክተዋል፡፡ መንግሥት ለግሉ ዘርፍ እየሰጠ ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥልም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ቻይና አረንጓዴ ኢኮኖሚያዊ እድገት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጋር የሚጣጣም መሆኑንም ጠቁመዋል።

ሁለቱ ሀገራት ቃላቸውን ወደ ተግባር በመቀየር ላይ የሚገኙና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ በመገንባት ምሳሌ የሚሆን ሥራ እየሠሩ ነው ያሉት አምባሳደር ቸን፤ የቻይና ባለሀብቶች የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ስኬት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እያበረከቱ መሆኑን ገልጸዋል።

ሲኖ አልሙኒየም ማኑፋክቸሪንግ የተባለው ኩባንያ ፕላስቲክ ተረፈ ምርቶችን ወደ ፋይበር በመቀየር ለተለያዩ ምርቶች ግብዓትነት እንዲውል እያደረገ ነው። በዚህም በሺህ የሚቆጠር ቶኖች ዓመታዊ ምርት ላይ ደርሷል። ኤምባሲውም ሌሎችም የቻይና ኩባንያዎች በአረንጓዴ ዐሻራ ጋር የሚጣጣም ሥራዎች ላይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው እንደሚያበረታታ አብራርተዋል።

የሁለቱን ሀገራት ሁለንተናዊ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ቅድሚያ ሰጥተው እንደሚሠሩ ጠቅሰው፤ ቻይና ቀጣናው ላይ መተማመን ላይ የተመሠረተ አስተማማኝና ዘላቂ ሠላም እንዲሰፍንም የበኩሏን አስተዋፅዖ እንደምታበረክትም ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ጠንካራ ሠራተኛ ሆነ ሕዝብ እንዲሁም ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ያላት ሀገር መሆኗን ያስታወሱት አምባሳደር ቸን፤ ይህም በንግድ፣ በኢንቨስትመንት፣ በመሠረተ ልማት በሌሎችም ዘርፎች በትብብር ለመሥራት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር አመላክተዋል።

እነዚህም በቻይናና በኢትዮጵያ መሪዎች መካከል መግባባት ላይ የተደረሰባቸው ጉዳዮች ወደ ተግባራዊ እርምጃ ለመግባት መሠረት የሚጥሉ መሆናቸውን ገልጸው፤ የቻይና የግብርና ባለሙያዎች ወደኢትዮጵያ መጥተው እየሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

ቻይና ቡናን ጨምሮ ወደ ሀገሯ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን እያሳደገች መሆኑን ጠቅሰው፤ የቻይና ባለሀብቶች ማዳበሪያን ጨምሮ ለኢትዮጵያ አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ግብዓቶችን ለማቅረብ እየሠሩ ነው ብለዋል።

በጥቅሉ ቻይና በግብርና ልማት ከኢትዮጵያ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ልምድ ስላላት ዋነኛዋ የኢትዮጵያ አጋር ሆና እንደምትቀጥል ገልጸዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ በቢሾፍቱ በምትገነባው ግዙፍ የአየር ማረፊያ ግንባታ ላይ ለመሳተፍ የቻይና ድርጅቶች የአዋጭነት ጥናት በማከናወን ላይ መሆናቸውንም አምባሳደሩ ጨምረው ገልጸዋል።

# ምክክሩ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዘላቂ እና መሠረታዊ መፍትሔ ለማምጣት ሁሉን አካታች እና አሳታፊ የሆነ ሀገራዊ ምክክር በማድረግ መግባባት ላይ ለመድረስ ኮሚሽኑ መቋቋሙንም አስታውሰዋል።

ኮሚሽኑ እንደ ሀገር ላሉት አለመግባባቶች እና የሀሳብ ልዩነቶች መንስኤ የሆኑ እጅግ መሠረታዊና ሀገራዊ የሆኑ አጀንዳዎችን እንደሚቀርጽ የተናገሩት ዋና ኮሚሽነሩ፤ በምክክር መግባባት ላይ እንዲደረስባቸው በማድረግ ተፈጻሚነታቸውን ጭምር እንደሚከታተል አመላክተዋል።

ከታኅሣሥ 7 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ለዘጠኝ ተከታታይ ቀናት በኦሮሚያ ክልል በሚካሄደው የአጀንዳ ማሰባሰብ መድረክ ኮሚሽኑ የኦሮሚያ ክልል አጀንዳዎችን እንደሚሰበስብ የገለጹት ዋና ኮሚሽነሩ፤ በዋናው ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ ኦሮሚያ ክልልን ወክለው የሚሳተፉ ተወካዮች እንደሚመረጡም ተናግረዋል። ለዘጠኝ ቀናት በሚደረገው የአጀንዳ ማሰባሰብ የውይይት መድረክ ክልሉን ወክለው በዋናው ሀገራዊ የምክክር ጉባኤ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ 320 ተወካዮች እንደሚመረጡ ነው የገለጹት።

በሁለት ምዕራፎች በሚደረገው መድረክ በመጀመሪያው ምዕራፍ ከ356 ወረዳዎች የተውጣጡ ከሰባት ሺህ በላይ የኅብረተሰብ ተወካዮች እንደሚሳተፉ አመልክተው፤ በሁለተኛው ምዕራፍ የኅብረተሰብ ተወካዮች፣ ልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት፣ ሀገር አቀፍና በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የተቋማትና ማኅበራት ተወካዮች፣ ታዋቂና ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች እና ሦስቱ የመንግሥት አካላት እንደሚሳተፉበት ገልጸዋል፡፡

የኦሮሚያ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ ሲጠናቀቅ የሚቀሩት አማራ እና ትግራይ ክልሎች ብቻ መሆናቸውን ያስታወሱት ዋና ኮሚሽነር፤ ይህም በወረዳ ደረጃ የአጀንዳ ስብሰባ የተጠናቀቀባቸውን ወረዳዎች ከ615 ወደ 971 ከፍ እንደሚያደርገው ጠቁመዋል።

መድረኩ የኦሮሚያ ክልል ተሳታፊዎች ላለመግባባት ምክንያት የሆኑ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት ለችግሮቹ መፍትሔ የምትፈልጉበት ታሪካዊ መድረክ ነው ያሉት መስፍን አርዓያ (ፕሮፌሰር) ተሳታፊዎች ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን አጀንዳዎች በመጠቆም በምክክር ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ጥሪ አቅርበዋል።

# ፈርጀ ብዙው የተኪ ምርቶች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በሀገር ውስጥ ማምረት እየተቻለ በርካታ ምርቶች ከውጭ ሲገቡ ለሠለጠኑ ሀገራት ጥገኛ መሆንን እንደሚያስከትል የሚገልጹት ፕሮፌሰሩ፤ ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት የሀገሪቷን የኢኮኖሚ እድገት ያሳልጣል። ተኪ ምርቶችን ለማምረት ሲባል አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና ማሽነሪዎች የሚገቡ በመሆኑ አዳዲስ የሥራ ዕድሎች እንደሚፈጠሩም ይገልጻሉ።

ከውጭ ምርቶችን ለማስገባት ሲወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሪ እንደሚያስቀር የሚገልጹት ምሑሩ፤ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች መተካት የውጭ ምንዛሪ ጥገኝነትንም ያስቀራል ይላሉ ።

ሀገር የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ሲባል ባደጉት ሀገራት ላይ ጥገኛ ትሆናለች የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ አብዛኛው የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በሀገር ውስጥ ምርት ማሟላት ከተቻለ የውጭ ምንዛሪ ጥገኝነቱ እንደሚቀንስም ይናገራሉ።

ለአምራቾች የተለያዩ ማበረታቻዎችን በመስጠት አምራቾች ወደ ማምረት እንዲገቡ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ ይህ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች እንዲያድጉ በማድረግ ሀገሪቷ በኢንዱስትሪ የበለፀገች እንድትሆን ያደርጋታል ነው ያሉት።

ተኪ ምርቶች እዚሁ በሀገር ውስጥ ጉልበት እና ሀብት የሚመረቱ በመሆኑ ዋጋቸው ከውጭ ከሚመጡ ምርቶች እንደሚቀንሱ የሚናገሩት ፕሮፌሰሩ፤ ይህ ደግሞ ዋጋን በማረጋጋት የራሱ ትልቅ አስተዋፅዖ አለው ይላሉ።

እንደ ብራዚል፣ ሜክሲኮ እና አርጀንቲና የመሳሰሉ ሀገራት በመጀመሪያ ተኪ ምርቶችን ምግብ ላይ በማተኮር በምግብ እራሳቸውን ለመቻል ነው የሠሩት ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ አሁን ላይ ሀገራቱ የኤሌክትሮኒክስ ውጤቶችንና ሌሎች ነገሮችን በማምረት ከውጭ የሚያስገቡትን አብዛኛውን ነገር በማስቀረት ሀገራቸውን ማሳደጋቸውን ነው የገለጹት።

ኢትዮጵያም በቅድሚያ ምግብ ነክ የሆኑ ነገሮችን በሀገር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ እንዲመረቱ በማድረግ የሕዝቡን ፍላጎት በማሟላት የተረፈውን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ መሆን ትችላለች የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ ከምግብ ፍላጎታችን በራሳችን ኢንዱስትሪ ምርቶች ከሸፈንን በኋላ የኤሌክትሮኒክስ እና ማሽኖችን በሀገር ውስጥ በማምረትም ተኪ ምርቶችን ማሳደግ እንደሚቻልም አመላክተዋል።

እንደ ሀገር አሁን ላይ ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት ላይ እየተሠራ ያለው ሥራ በመልካም ሁኔታ ላይ ነው የሚሉት ምሑሩ፤ በቀጣይም ገጠራማ አካባቢዎች ድረስ በመውረድ መታረስ የሚችል መሬት ሳይታረስ እንዳይቀር መሠራት አለበት ይላሉ።

ኢትዮጵያ ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት በኢኮኖሚ እራሷን በመቻል ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ከተላቀቀች ያደጉት ሀገራት በውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ አይገቡም። ኢትዮጵያ የፀጥታ ሁኔታው ላይ በመሥራት አስተማማኝ ሠላም እንዲፈጠር በማድረግ ምርትና ምርታማነት ላይ ማተኮር እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህርና ተመራማሪ አጥላው ዓለሙ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደሚሉት፤ አንድ ሀገር ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት መቻሏ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ የጎላ ነው። ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት ሲቻል ሀገር የራሷን የሰው ኃይል እና ጥሬ እቃዎች በሚገባ መጠቀም ትችላለች። ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ልምድም ይዳብራል።

ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ የማምረት አስፈላጊነት ብዙ ቢሆንም እንደ ኢትዮጵያ ተግባራዊነቱ ላይ ያለው አፈጻጸም ዝቅተኛ ነው ብለው የሚያምኑት አጥላው (ዶ/ር)፤ ተኪ ምርቶችን ማምረት በሚቻለው ልክ ማምረት አለመቻሉ ኢትዮጵያ እስከአሁን ማግኘት ያለባትን ጥቅም እንዳታገኝ አድርጓታል ይላሉ።

ኢትዮጵያ ከውጭ የምታስገባቸውን ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለማምረት የአቅም እና የእውቀት ችግር የለባትም የሚሉት ምሑሩ፤ አሁንም ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት ተነሳሽነቱ መጨመር አለበት። ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለማምረት የተጀመረው እንቅስቃሴም በቂ ባለመሆኑ ማደግ እንዳለበትም ይናገራሉ።

የምግብ ሸቀጦች፣ አነስተኛ ሸቀጣሸቀጦች እና አልባሳት እዚሁ በሀገር ውስጥ በማምረት ከውጭ የሚገቡትን ማስቀረት እንደሚቻል ተናግረው፤ ቀስ በቀስ አብዛኛው ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ መተካት እንደሚቻልም ይገልጻሉ።

ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ሀገር ውስጥ በሚመረቱ ተኪ ምርቶች መተካት ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት ምሑራኑ ይስማማሉ። ለዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገትም ፋይዳው የጎላ መሆኑ ነው የገለጹት።

ምሑራኑ እንደሚሉት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተጀመረው "ኢትዮጵያ ታምርት" ንቅናቄ በርካታ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች የመተካት እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ቢቀጥል የውጭ ምንዛሪን በማስቀረት፣ ለዜጎች የሥራ ዕድልን በመፍጠር እና አዳዲስ ቴክኖሎጂን ከማምጣት አንጻር ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ትልቅ አስተዋፅዖ ያበረክታል። ሀገርም የዕድገት ግስጋሴዋ ዘላቂና አስተማማኝ ይሆናል። የሥራ አጥነትም ችግርም በሂደት እየተፈታ ይሄዳል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የቀጣናዊ ትስስሮሽ ታላቅ መገለጫ!

የአፍሪካ የነፃነት ዓርማ፤ የጥቁር ሕዝቦች መኩታ እና የአልሸነፍ ባይነት ተምሳሌት የሆነችው ኢትዮጵያ ከጥንት እስከ ዛሬ የጋራ ተጠቃሚነት መርሕን በማንገብ ለተግባራዊነቱ ስትንቀሳቀስ ቆይታለች:: በዚሁ ጥረቷም በርካቶች ከቅኝ ግዛት ተላቀው ነፃ ሀገር እንዲሆኑና ነፃ ኢኮኖሚም እንዲገነቡ የበኩሏን ድርሻ ስትወጣ ቆይታለች:: ከአፍሪካ አንድነት ምሥረታ ጀምሮ አፍሪካ በኢኮኖሚ ጭምር የተዋሐዱ እንዲሆኑ አበክራ ሠርታለች:: ለዚህም አንዱ ማሳያ አፍሪካውያንን በኢኮኖሚ ለማስተሳሰር በማሰብ በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን እንዲቋቋም አድርጋለች::

ይኸው ጥረቷ ቀጥሎ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን በማዕከልነት በማስተባበር በኢኮኖሚ፤ በሠላምና ፀጥታ እንዲሁም በባሕልና ታሪክ ላይ አካባቢያዊ ጥምረት እንዲፈጠር የበኩሏን አስተዋፅዖ ማበርከት ከጀመረች ውላ አድራለች:: የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀዳሚ ትኩረትም የጎረቤት ሀገራት በመሆናቸው የጎረቤት ሀገራትን በተለያዩ ዘርፎች ለማስተሳሰር ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች:: ከዚህ ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው የኃይል አቅርቦት ዘርፍ ነው::

ኢትዮጵያ ከ13 ዓመታት በፊት የጀመረችው ታላቁ የዓባይ ግድብ ወደ መገባደዱ ደርሷል:: ግድቡ ሙሉ ለሙሉ ከመጠናቀቁ በፊት ከወዲሁ ለጎረቤት ሀገራት ጭምር የኃይል ምንጭ በመሆን ምሥራቅ አፍሪካን በማስተሳሰር ላይ ይገኛል:: ግድቡ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅም የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት አስተማማኝ የኃይል ምንጭ እንዲያገኙ ከማስቻሉም በላይ የቀጣናውን ሀገራት የጋራ ኢኮኖሚ እንዲገነቡ በር የሚከፍት ይሆናል::

የምሥራቅ አፍሪካ ከፍተኛ የኃይል እጥረት ከሚታይባቸው አካባቢዎች አንዱ ነው:: በቀጣናው የሚገኙት ሀገራት ከፍተኛ የኃይል እጥረት ያለባቸው በመሆኑ እና በዚህም የተነሳ ኢኮኖሚያቸው በአዝጋሚ ሂደት ውስጥ የሚገኝ ነው:: ሀገራቱ አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት እስካላገኙ ድረስ የዜጎቻቸውን ሕይወት ማሻሻል ካለመቻላቸውም ባሻገር ለፀጥታ ችግር፤ ለሕገወጥ ስደት እና ለሽብርተኝነት ይጋለጣሉ::

ይህንኑ በመረዳትም ኢትዮጵያ ለሱዳን፤ ለደቡብ ሱዳን፤ ኬኒያ፤ ለጅቡቲ ኃይል እያቀረበች ሲሆን በቀጣይም ወደ ታንዛኒያ፤ ዑጋንዳ እና አለፍ ሲልም ወደ ደቡብ አፍሪካ ድረስ የኤሌክትሪክ ኃይል ለመላክ ዝግጅቶችን በማድረግ ላይ ትገኛለች:: ይህ ደግሞ ቀደም ሲል ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ነፃነት ግንባር ቀደም ሚናዋን እንደተወጣች ሁሉ የአፍሪካ ሀገራት የኢኮኖሚ ነፃነትም እንዲጎናጸፉ የማይተካ ሚና በመጫወት ላይ መሆኗን የሚያመላክት ነው::

ከኃይል አቅርቦቱ ጎን ለጎንም ንጹሕ የመጠጥ ውሃ ለጎረቤት ሀገራት በተለይም ለጅቡቲ በመላክ ቀጣናዊ ትስስሮሽን በማጎልበት ላይ ትገኛለች:: ከ258 ኪ.ሜ በላይ የውሃ መስመር ዝርጋታ በማከናወን ኢትዮጵያ በየቀኑ ለጅቡቲ እያቀረበች ያለችውን ከ20ሺህ እስከ 30ሺህ ኪዩቢክ ሜትር ንጹሕ የመጠጥ ውሃን ወደ 100 ሺህ ኪዩቢክ ሜትር ለማሳደግ እየሠራች ትገኛለች:: ይህም ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብቶቿን ጭምር በመስጠት ቀጣናዊ ትስስሩን ለማጠናከር እየሠራች መሆኑን አመላካች ነው::

ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ያላትን ሚና በአግባቡ ለመወጣትም ነፃ የንግድ ቀጣና በድሬዳዋ መሥርታለች። ይህ የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ደረቅ ወደብን ከዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት፣ ከባቡርና ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር በማቀናጀት፣ ምርቶችን በቀላሉ ወደ ጎረቤት ሀገራት ለመላክ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ነው::

ከዚሁ ጎን ለጎንም የአፍሪካ አሕጉራዊ ነፃ ንግድ ቀጣናን /AfCFTA/ በማጠናከር ረገድ የማይተካ ሚና እየተጫወተች ትገኛለች:: በፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ መነሻነት የተመሠረተው አሕጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ካሉት መርሆዎች ውስጥ “የአንድን ሀገር ምርት ከሌላው ሀገር ምርት ጋር እኩል ማስተናገድ”፣ “የሀገር ውስጥ ምርትን ከአባል ሀገራቱ ከሚገቡ ምርቶች ጋር እኩል ማስተናገድ” የሚሉት ይገኙበታል:: በዚህ መሠረትም ለሀገራችን ኢንዱስትሪዎች እና የንግድ ማኅበረሰብ አካላት ምርቶቻቸውን በሀገር ውስጥም በሌሎች የአፍሪካ ሀገራትም እኩል የመወዳደር ዕድል ከመስጠቱም ባሻገር ከአፍሪካ ሀገራት ጋር በጋራ የመነገድን ዕድል የሚሰጥ ነው::

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ኅብረት 2063 አጀንዳ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ የሆነውን ቀጣናዊ ትስስርን የማጠናከር ተግባር በውጤታማነት እየተወጣች ትገኛለች:: በተለይም በኃይል አቅርቦት፤ በግብርና ምርት እና ስንዴን ከራሷ አልፎ ወደ ጎረቤት ሀገራት መላክ መቻሏ ተጠቃሽ ያደርጋታል:: በሌላም በኩል ቀጣናዊ እና አሕጉራዊ ትስስርን በመፍጠር የአፍሪካ ኅብረት የቀመለትን ዓላማ ለማሳካት የበኩሏን ሚና እየተወጣች ትቀጥላለች!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው::በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የአፍሪካውያን የኢትዮጵያ ወራት!

**እስመለዓለም**

የያዝነው ታኅሣሥ እና መጪው ጥር ለኢትዮጵያ በተለይ ደግሞ ለአዲስ አበባ ብቻ ልዩ ስፍራ አላቸው:: ወራቱ የአፍሪካ ኅብረት ዋና መሥሪያ ቤት መገኛዋ አዲስ አበባ በየዓመቱ በእነዚህ ወራት የኅብረቱን የመሪዎች ጉባኤና ሌሎች ተያያዥ ስብሰባዎች ይስተናገዱባቸዋል::

እንደሚታወቀው የአፍሪካ ኅብረት በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ የመሪዎች ስብሰባውን ያካሂዳል፤ ከእነዚህ ስብሰባዎች በጥር ወር የሚካሄደው ስብሰባ በመደበኛነት የሚካሄደው ጽሕፈት ቤቱ በሚገኝባት አዲስ አበባ ነው:: ኢትዮጵያም ይህን ታላቅ መድረክ ስታዘጋጅ ኖራለች::

ሰኔ ወር አካባቢ የሚካሄደውን የመሪዎች ስብሰባ የሚያስተናግዱት ሌሎች አባል ሀገሮች ናቸው:: ይሁንና አንዳንድ ጊዜ አስተናጋጅ ሀገሮች ማስተናገድ የማይችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር ስብሰባው የሚካሄደው እዚሁ አዲስ አበባ ላይ ነው:: አዲስ አበባ አንዳንዴ በዓመት ሁለቴ የመሪዎች ስብሰባውን ልታስናግድ ትችላለች:: በዚህ ምክንያት ሀገሪቱ የኅብረቱን የመሪዎች ስብሰባዎች በማስተናገድ በእጅጉ ትታወቃለች::

ሀገሪቱ የኅብረቱን የመሪዎች ስብሰባ ብቻ አይደለም ስታስናግድ የኖረችው:: ከዚህ ታላቅ መድረክ ጎን ለጎን በርካታ አሕጉራዊ፣ ክፍለ አሕጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎች የሚካሄዱ እንደመሆናቸው እነዚህን ስብሰባዎች ሲሉ የሚመጡ እንግዶችን ተቀብላ በቂ ማረፊያ አዘጋጅታ፣ ሲወጡና ሲገቡ እያጀበች ትሸኛለች::

እናም እነዚህ ስብሰባዎች የሚካሄዱባቸው የታኅሣሥና የጥር ወራት በአፍሪካውያኑ ልብ ውስጥ የተቀመጡ ናቸውና ለእነሱም ወራቱ ልዩ ስፍራ አላቸው ብሎ መናገር ይቻላል። በኢትዮጵያ ለስብሰባ የሚቀመጡባቸው፣ የሚጓዙባቸውና በኢትዮጵያ አንዳንድ ቦታዎችን የሚጎበኙባቸው ወራት እንደመሆናቸው በእነዚህ ወራት ስለኢትዮጵያ ብዙ ያወጣሉ ያወርዳሉ:: በኢትዮጵያ መሰብሰብ፣ ወደ ኢትዮጵያ መምጣትና በኢትዮጵያ መቆየት፣ ወደ ኢትዮጵያ ስለመሄድ ማሰብ ከኢትዮጵያ ስለሚገዙት ወደኢትዮጵያ ይዘው ስለሚሄዱት ማሰብ የአፍሪካውያኑ የእነዚህ ወራት ማሰብ ማሰላሰል ናቸው:: እናም ወራቱ የአፍሪካውያን የኢትዮጵያ ወራት ሊባሉ ይችላሉ::

በእነዚህ ወራት በተለይ በጥር ወር በርካታ የአፍሪካ ሀገሮች ዲፕሎማቶች፣ በተለያዩ የአሕጉሪቱ ሀገሮች መቀመጫቸውን ያደረጉ የአፍሪካ ኅብረት የተለያዩ ተቋማት ኃላፊዎችና ሠራተኞች በእዚህ ታላቅ መድረክ ላይ ለመታደም ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ::

አፍሪካውያንን በአንድ ስፍራ ማግኘትን እንደ መልካም አጋጣሚ የሚጠቀሙ እንደ ተባበሩት መንግሥታት፣ ዓረብ ሊግ፣ አውሮፓ ኅብረት፣ አሁን ደግሞ ብሪክስ የመሳሰሉት ተቋማት፣ እንደ ዓለም ባንክ፣ የዓለም የገንዘብ ድርጅት ፣ የዓለም ጤና ድርጅትና የመሳሰሉት ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም በእዚህ ወቅት ኢትዮጵያ መዳረሻቸው ናት:: በዚህ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ ሊመጡ የሚችሉ ተቋማትን ዘርዝሮ መጨረስ አይቻልም፤ አትዮጵያ በእነዚህ ወራት አያሌ አፍሪካውያን ታስተናግዳለች::

ስብሰባዎቹን የማስተናገድ ኃላፊነቷን በሚገባ በመወጣት ዓመታትን ዘልቃለች:: በፀጥታና ሠላም፣ በአካባቢ ፅዳትና ንጽሕና፣ በሆቴልና ስብሰባ አዳራሾች ዝግጅት፣ ወዘተ ሰፊ ዝግጅት በማድረግ ነው እንግዶቿን ተቀብላ የምታስናግደው::

በዚህ ዝግጅት መንግሥት ብቻውን አይደለም የሚሠራው:: ከመላው ሕዝብ ከአዲስ አበባ ነዋሪዎች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ይሠራል:: ሕዝቡ በተለይ በአካባቢ ፅዳትና ንጽሕና በሠላምና ደኅንነት ጥበቃ ሲያከናወን የኖረው ተግባር ሊታወስ ይገባል::

የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫን ከአዲስ አበባ ለማውጣት ከፍተኛ ጥረት ይደረግ በነበረባቸው ዘመናት ሀገሪቱ ለስሟ የማይመጥን የነበረውን/በእርግጥም የሚያሳማ አልነበረም ማለት አይቻልም/የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ችግርና የንጽሕና ጉድለት ለመፍታት በየዓመቱ ይካሄድ የነበረው ዘመቻ ሊዘነጋ አይገባም:: ምንም እንኳ ችግሩ በሂደት በወሳኝ መልኩ የተቀረፈ ቢሆንም በዚህ ወቅት ግን ሕዝቡን በመያዝ ሰፊ የፅዳት ዘመቻ ይካሄድ እንደነበር ይታወሳል::

ምስጋና በደረቅ ቆሻሻ ላይ ለውጥ እንዲመጣ ላደረጉት የከተማዋ አስተዳደር፣ በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሥራ የተሠማሩ ማኅበራትና መላው ሕዝብ ያ የሀገሪቱን ስም ያጎደፈው የፅዳት ጉድለት ዛሬ ላይ አለ በሚባል ደረጃ አይስተዋልም::

በከተማ እየተካሄደ ያለው የኮሪደር ልማት ደግሞ ይህን ስኬት ታላቅ ከፍታ ላይ አድርሶታል:: የዘንድሮው የኅብረቱ ስብሰባ ሀገሪቱ በኮሪደር ልማት ወሳኝ ዋና ዋና መንገዶቿን ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ በቻለችበት ወቅት የሚካሄድ ነው::

የፌዴራል መንግሥት፣ የከተማዋ አስተዳደር ከተማዋን እንደ ስሟ ውብ ለማድረግ ተነሳሽነት ይዘው በመሥራታቸው ዘንድሮ እንዳለፉት ዓመታት ለአፍሪካ ኅብረት ሲባል የሚደረግ የፅዳት ዘመቻ የሚካሄድበት ሁኔታ ይኖራል ብዬ አልገምትም፤ አዲስ አበባ በዚህ በኩል ዝግጁና ዝግጁ ተደርጋለች::

አዲስ አበባ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ለጉባኤው እድምተኞች አዳዲስ ክስተቶችንም ይዛ መቅረቡን ተያይዛዋለች:: አፍሪካውያን ቅኝ ግዛትን አምርረው እንዲዋጉ በፓን አፍሪካኒዝም ጥላ ስር ይበልጥ እንዲሰባሰቡ ያደረገው የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ቀንዲል ተደርጎ የሚታየው የዓድዋ ድልን የሚዘክረውን የዓድል ድል መታሰቢያን ገንብታ አፍሪካውያንም ታሪካቸውን እንዲዘክሩ እነሆ ብላለች:: ከተማዋ ቀደም ሲል ያልነበሩ ግዙፍ ፓርኮችን፣ አደባባዮችን፣ ሰፋፊ መንገዶችን ገንብታለች:: ሁሉም አፍሪካውያንን ሊቀበሉ ዝግጁ ናቸው:: እናም ዝግጁነቷ ከመቼውም ጊዜ ከፍተኛ ነው ብሎ መመስከር ይቻላል::

እንግዶች በዋናነት የሚተላለፉባቸው ጎዳናዎችና አደባባዮች ብቻም ሳይሆኑ ሌሎች በርካታ አካባቢዎች ፅዱና ውብ ተደርገዋልና ከአንዳንድ የማጠናቀቂያ ሥራዎች በስተቀር የዝግጅቱ አንድ ትልቅ ሥራ አስቀድሞ ተጠናቋል ማለት ይቻላል::

መንገዶች፣ አደባባዮች ፅዱ ብቻ ሳይሆን ውብም ተደርገዋል:: የኮሪደር ልማቱ በተካሄደባቸው ጎዳናዎች በሙሉ የአረንጓዴ ስፍራዎች ተካተዋል:: ሣር፣ አበቦችና ዛፎች የተካተቱባቸው የአረንጓዴ ስፍራዎቹ እንደ ሀገሪቱ ባሕልና ወግ ቁጤማ የመነዝነዝ ያህል ሊታዩ የሚችሉ ናቸው::

በምሽት ወቅት ደግሞ ይበልጥ ውብ የሚያደርጓት የተለያዩ መብራቶች በጎዳናዎቿ በአረንጓዴ ስፍራዎቿ፣ በሕንጻዎቿና ዛፎቿ ላይ ጭምር በማድረግ ይበልጥ እንድታሸበርቅ ተደርጋለች:: እነዚህ የከተማዋ ውበቶች ከፋውንቴኖች በሚወጣው ልዩ ልዩ ትርዒት በሚያሳይ ውሃ ይበልጥ ደምቀዋል:: ለፀጥታዋ ካሜራዎችን ገጥማለች፤ በየአደባባዩና ግዙፍ መንገድ ዳርቻዎች መልእክቶችን እንዲያስተላልፉ የተገጠሙ ስክሪኖች ሌሎች ድምቀቶቿ ናቸው::

መገናኛ ብዙኃን ገና ከአሁኑ የኅብረቱን ቀደምት መሪዎች የሚያስታወሱ ዘገባዎችን ማቅረብ ጀምረዋል:: አፍሪካውያን በእጅጉ እየታወሱ ናቸው::

በሠላምና ፀጥታ በኩልም ቢሆን እንደዚያው ነው። ሀገሪቱ ቀድሞውንም ቢሆን በዚህ በኩል ያላት ዝግጁነት በሚገባ ይታወቃል፤ የተመሰከረለትም ነው:: ዘንድሮም ይሄው ተጠናክሮ ይቀጥላል:: በኮሪደር ልማቱ በየጎዳናዎቹ የተተከሉ የደኅንነት ካሜራዎች እንዲሁም የፀጥታ አካላት ዝግጁነት ይህንኑ ያመለክታሉ::

የኅብረቱ መሪዎች ስብሰባ ከጥር ወር አጋማሽ በኋላ የሚካሄድ ቢሆንም፣ ሌሎች አስቀድመው የሚካሄዱ ስብሰባዎች በርካታ ናቸው:: በመግቢያችን እንደጠቀስኩት ወራቱ የአፍሪካውያን የኢትዮጵያ ወራት ናቸው:: አያሌ አፍሪካውያን በእነዚህ ወራት በኢትዮጵያ ያገኛሉ:: እነዚህ ኢትዮጵያ ሁለተኛ ቤታቸው የሆኑት አፍሪካውያን ቆይታ ስኬታማ እንዲሆን ዝግጅቶቹ የራሳቸውን ሚና ሊጫወቱ ቢችሉም ሕዝብና መንግሥት እጅና ጓንት ሆነው መሥራታቸውን ማጠናከር ይኖርባቸዋል::

**ምስጋና በደረቅ ቆሻሻ ላይ ለውጥ እንዲመጣ ላደረጉት የከተማዋ አስተዳደር፣ በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሥራ የተሠማሩ ማኅበራትና መላው ሕዝብ ያ የሀገሪቱን ስም ያጎደፈው የፅዳት ጉድለት ዛሬ ላይ አለ በሚባል ደረጃ አይስተዋልም**

# ነፃ ሃሳብ

## የተቋማት አገልግሎት እና «ምስለ ተገልጋይ»

በየኔነው ስሻው

ከእለታት በአንዱ ቀን ነው፤ ግን ሩቅ ያልሆነ፣ ባሳለፍነው ወርሃ ሕዳር መገባደጃ ላይ የሆነ:: አንዲት የማስፈጽማት ጉዳይ ስለነበረችኝ አራት እና አምስት ተቋማትን፤ ያውም በክልልም፤ በፌዴራልም ደረጃ ያሉትን የመንግሥት ተቋማት ደጅ የመርገጥ እድል ገጥሞኝ ነበር:: ጉዳዬን ላስፈጽም ግን የየተቋማቱን ደጃፍ ከአንድ ጊዜ በላይ መድረስ ነበረብኝ:: በተለይ በሁለቱ ተቋማት የነበረኝ የጉዳይ የማስጨረስ ሂደት ነገሮችን ቆም ብሎ ማሰብ፤ የጉዳይ መግደያ (ማሳለጫ) አማራጮችን መመልከትም ግድ የሚሉ ነበሩ::

"ወፍ እንደ ሀገሯ ትጮኻለች" እንዲሉ፤ እኔም ጉዳዬን ተመላልሼ ማስጨረሱ ጊዜም፣ ጉልበትም፣ ገንዘብም ማባከን መሆኑን ስረዳ፤ እንደየከባቢው አሰራር መራመድ፣ በተለምዶው 'ጉዳይ ገዳይ' እየተባሉ የሚጠሩ ግለሰቦችን ማማተር ጀመርኩ። ለነገሩ እነርሱስ መች እስካማትር ጠብቀው፤ ቀድሞውኑ አግባብተው ነግረውና አስረድተውኝ ነበርና ወደነሱው ፊቴን አዞርኩ::

በቃ ከዚህ በኋላ ሁለትና ሦስት ቀናት የተመላለስኩበት ጉዳይ ሁለትና ሦስት ሰዓትን እንድጠብቅ እንኳን አላደረገኝም:: እንዴት ቢባል፤ የእኔም መልስ አላውቅም ነው:: ምክንያቱም እኔ ያወራሁት እና ጉዳዬን የጨረስኩት ከእነዚህ በተቋማት አካባቢ በማይጠፉት "ጉዳይ ገዳይ" ግለሰቦች አማካኝነት ነው::

እነርሱ ደግሞ እኔ በሁለትና ሦስት ቀን ሊደርሰኝ ያልቻለውን ጉዳይ ፈጻሚዬጋ የመድረስ መንገድ ማፋጠኛ (በእነሱ አጠራር የወረፋ/የተራ) ክፍያ ነው የጠየቁት:: እኔ የተራ ያሉትን ክፍያ ፈጸምኩ፤ እነሱም ጉዳዬን ፈጸሙልኝ ወይም አስፈጸሙልኝ። ይሄ ቀለል ያለው፣ እኔም ከመመላለሱ ይልቅ የተሻለ አዋጪ ይሆናል ብዬ ድካሜን ለመቀነስ ስል ያደረኩት ነው:: መቼም ሲቸግር ከመጥፎም የተሻለውን መጥፎ ይምርጡ የለ:: እንደዛ ነው የሆነው::

ክስተቱ አያሌ ጥያቄዎችን በውስጤ እንዲ መላለሱ አድርጓል:: ምክንያቱም፣ ምን ያህል ተገልጋይ በዚህ መልኩ አልፎ ጉዳዩን አስፈጽሟል? ምን ያህሉስ ይሄን መንገድ ማለፍ ሳይችል ተንገላቷል? ምን ያህሉስ በጉዳዩ ላይ ቅሬታውን አሰምቶ መፍትሄ አግኝቷል? ወይስ አቤቱታው በዝምታ ታልፏል? በዚህ መልኩ ከመጥፎ መካከል የተሻለው መጥፎ እንዲመረጥ የሚያደርግ የተቋማት ከባቢ ለምን ተፈጠረ? ችግሩስ በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት አይታወቅምን? ከታወቀስ ለምን ተገቢው እርምትና እርምጃ ሊወሰድ አልቻለም?... የሚሉ መልስ አልባ ጥያቄዎች አዕምሮዬን እረፍት ነሱት::

እኔም ለጊዜው ማለፍ የሌለበት ጉዳዬን በጉዳይ ገዳዮች በኩል ብፈጽምም፤ እነዚህ ረፍት የነሱኝና ያልተፈጸሙ ጥያቄዎቼን ይገዬ ማብሰልሰል አላቆምኩም:: አካባቢውን ማጤን ጀመርኩ፣ በጉዳይ ገዳይነት የተሰማሩት አካላትን መለየት ጀመርኩ:: በየተቋማት አካባቢ በሊስትሮ ስም፣ በፓርኪንክ ሰራተኛ ስም፣ በደላላ ስም፣ አለፍ ሲልም በየተቋማቱ ደመወዝ ተከፋይ በሆኑ ሰራተኞች ለምሳሌ በጥበቃ ሰራተኛ ስም፣... በነጻነት ያለ ፍርሃትና መሳቀቅ የሚምነሸነሹ ግለሰቦች መሆናቸውን ተገነዘብኩ::

በተለያየ አጋጣሚ እንደሰማሁትም፤ በየሚዲያው እንዳደመጥኩትና እንዳነበብኩትም፤ እነዚህ ጉዳይ ገዳይ ግለሰቦች፤ ከበር መግቢያ ወረፋ/ሰልፍ መጠበቂያ ካርድ ጀምሮ እስከ ቢሮ ውስጥ ጉዳይ የማስጨረስ ሚናን የሚወጡ ናቸው። የወረፋ ካርድ ይዘው የሻይ እያተረፉ ከሚሸጡት፤ የውስጥ ጉዳይ ገድለው በኮሚሽን እስከሚሰሩት የተሳሰሩም ናቸው::

ደረጃቸው ሊለያይ ይችል ይሆናል እንጂ፣ ይሄን መሰል አሰራር በቀበሌዎች፣ በወረዳዎች፣ በክፍለ ከተማና ዞኖች፣ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ በቢሮዎች እና ፌዴራል ተቋማት በሁሉም ቦታና ሥፍራ እንደ አሸን የፈሉ ናቸው:: ለዚህም ይመስላል 'ዜጎች መታወቂያን ከማውጣት ጀምሮ ወደ መንግሥት ተቋማት በሚኖራቸው ጉዳይ ሁሉ እጅ እጃቸው የሚታይበት፤ እጃቸው ካልተፈታም ጉዳያቸው የሚታሸበት አሰራር "በሕግ የተፈቀደ" አስመስሎታል'

**ከመጥፎ መካከል የተሻለው መጥፎ እንዲመረጥ የሚያደርግ የተቋማት ከባቢ ለምን ተፈጠረ? ችግሩስ በሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት አይታወቅምን? ከታወቀስ ለምን ተገቢው እርምትና ርምጃ ሊወሰድ አልቻለም?... የሚሉ መልስ አልባ ጥያቄዎች አዕምሮዬን እረፍት ነሱት**

የሚል ሀሳብ ከብዙዎች መደመጡ::

አንዳንዴም በወሳኝ ኩነት አገልግሎት መስጫዎች፤ በመንጃ ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎት ማግኛ ቦታዎች፤ በሆስፒታሎች፤ በኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ባሉ አገልግሎቶች፤ ከንግድ እና ገቢ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች፤ በትራንስፖርት እና ሌሎችም የአገልግሎት አካባቢዎች ዜጎች በብዛት ቅሬታም፣ ምሬትም የሚያሰሙባቸው ስለመሆኑም በተደጋጋሚ በየሚዲያዎች ይገለጻል::

በአዲስ ዘመን ጋዜጣም በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ያሉ የአገልግሎት ችግሮችን፤ በየተቋማቱ የተሰማሩ ጉዳይ ገዳይ አካላትን፤ የዜጎችን ቅሬታና ምሬትን፤ የየተቋማቱን አሰራርና ችግሮችን፤... ደርሶ ሲዘግብ፤ የመፍትሄው አካል ለመሆን ከፍ ያለ ኃላፊነቱን ሲወጣ እንደቆየም በየጊዜው ከጋዜጣው ያነበብኳቸው ዜናዎች፣ ኤዲቶሪያሎች፣ ነጻ ሃሳቦችና አርቲክሎች ጭምር ሕያው ማሳያ ናቸው::

ከዜጎች የቅሬታ ድምጾች እና ከዜና ዘገባዎች ባሻገርም፣ በተለያየ ሁኔታ እና የመድረክ አጋጣሚዎች የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጭምር ስለ ችግሩ ሲናገሩ፤ ችግሩን ለመፍታት ቃል ሲገቡም፤ የችግሩ ተዋናዮችን ሲያስጠነቅቁም፤ ዜጎች ችግሩን ከመፍታት አኳያ ተባባሪነታቸውን በተግባር እንዲገልጡ ሲማጸኑም መስማት የተለመደ ነው::

ይሁን እንጂ ከትናን ዛሬ የችግሩ አይነት እና ስፋት ከፍ እያለ፤ የዜጎች አገልግሎት የማግኘት እድልም "በተፈታ እጅ ልክ እየተመነዘረ" የመጓዝ አዝማሚያው ልምምድ እየሆነ፤ አገልግሎትን በገንዘብ የመግዛት ልምምዱም በሕግ የተፈቀደ እስኪመስል የአደባባይ ተግባር እየሆነ መጥቷል::

አንድ ዜጋ የቀበሌ መታወቂያ ወይም የዜግነት መገለጫውን ፓስፖርት ለማውጣት ቀበሌም ሆነ ኢምግሬሽን ሲሄድ፤ ከእሱ የሚጠበቀውን ነገር እስካሟላ ድረስ ጉዳይ ገዳይም ሆነ እጅ መንሻ ከፊቱ ቆመው የይለፍ ፈቃድ ሰጪዎች ሊሆኑበት አይገባም:: አንድ ግለሰብ ክቡር የሆነውን የሰው ልጅም ሆነ ሃብት ንብረትን ይዞ የሚንቀሳቀስበትን የመንጃ ፈቃድ ማስረጃ ለማግኘት የሚጠበቅበትን እስካሟላ፤ እውቀት፣ አቅምና ክህሎቱን እስከጨበጠ ድረስ የግድ ጉቦ መክፈል አይጠበቅበትም::

አሁን አሁን ግን እንዲህ አይነቶቹም ሆኑ ሌሎች የመንግስታዊ አገልግሎቶች አንድም በጉዳይ ገዳይ ስም በተሰየሙ ግለሰቦች፤ ካልሆነም በቀጥታ ለጉዳይ ፈጻሚዎች በሚለገስ የእጅ መንሻ ላይ ተመስርተው የሚፈጸሙ እየሆኑ መጥተዋል:: ይሄ ደግሞ ሕዝብ እና መንግስት መካከል ያለውን ትምምን የሚሸረሽር፤ ሕዝብ በመንግስት ተቋማት ላይ ያለውን የባለቤትነትና የተገልጋይነት መንፈስ የሚያዳክም ስለመሆኑ እማኝ መጥቀስ አያሻውም።

በዚህ ረገድ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተከናወነ የዳሰሳ ምልከታ በየተቋማቱ እንዲህ አይነት ችግሮች ስለመታየታቸው በክብርት ከንቲባዋ አንደበት ሲነገር ሰምተናል:: ከንቲባዋ ይሄን ችግር ባሳወቁበት ወቅት የየተቋማት ኃላፊዎችን አስጠንቅቀዋል፤ ኃላፊነታቸውን መወጣት ካልቻሉና ሕዝቡን ለማገልገል ቁርጠኝነቱን ካጡ በራሳቸው ጊዜ የኃላፊነት ወንበራቸውን እንዲለቁ መክረው፤ ይሄን ማድረግ ባልቻሉና በሕዝብ ላይ የሚቆምሩ ሲገኙም ተገቢው እርምጃ እንደሚወሰድ አስገንዝበውም ነበር::

እንደ ኃላፊዎች ሁሉ በየቦታው ሕዝብን እንዲያገለግሉ የተቀመጡ ምንደኛ ሰራተኛና ባለሙያዎችም፣ በሕዝብ ገንዘብ እየኖሩ መልሰው ሕዝብን ለመበዝበዝና ለማማረር የሚታትሩበትን አካሄድ ሊያርሙ፤ ካልሆነም አስፈላጊው እርምትና ማስተካከያ እንዲሁም እርምጃ እንደሚወሰድ አስጠንቅቀዋል::

ምክንያቱም በዚህ መልኩ ራሳቸውን በገንዘብ የሚለኩ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ክፉ ምግባር፤ በብዙ መልኩ ለሕዝቦች አገልግሎት ራሳቸውን ሰጥተው የሚሰሩ ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን ስምና ገጽታም የሚያቆሽሽ ነው:: በመሆኑም ይሄን አይነት አስቀያሚም፣ አስነዋሪም ተግባር በመንግስት ተቋማት ሊኖር፤ የሕዝብን እምነትና የተገልጋይነት ስሜትም እንዲሸረሽር እድል ሊሰጥ አይገባም::

በዚህ ረገድ እንደ ከተማ አስተዳደር ችግሩን ከመፍታት አኳያም ጅምር ሥራዎች መኖራቸው እሙን ነው:: ይሁን እንጂ ጅምር ሥራው ከችግሩ ስፋትና አይነት እንዲሁም ተለዋዋጭነት አኳያ ብዙ የሚቀረው እና ከፍ ያለ ቁርጠኝነትንም የሚጠይቅ ነው:: እናም እንደ ከተማ አስተዳደር ያለው ጅምር ለሌሎችም ዓርዓያ ሊሆን በሚያስችለው መልኩ ሊጠናከር፤ አስተማሪም ሆኖ የከተማዋን ሕዝብ ከአስተዳደሩ ጋር ያለውን ትምምን ከፍ ወዳለ ደረጃ የሚያሸጋግር መሆን ይጠበቅበታል::

እንደ አዲስ አበባ ከተማ ያለውን በማሳያነት ለመጥቀስ ሞከርኩ እንጂ፣ ቀደም ብዬ እንደጠቆምኩት ችግሩ ደረጃው ቢለያይም በሁሉም አካባቢዎች፣ በሁሉም እርከኖችና ተቋማት የሚታይ ነው:: ይሄ ደግሞ እንደ ሀገር በመንግሥታዊ አገልግሎቶች ላይ ስብራትን የሚፈጥር፤ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደቱም ላይ አሉታዊ ጫናን የሚያሳድር መሆኑ እሙን ነው::

የብልፅግና ፓርቲም፣ በትረ መንግሥቱን ጨብጦ ሀገር እንደሚመራ መንግስት ችግሩን ተገንዝቦታል:: በቅርቡም በተለያዩ አካባቢዎችና ተቋማት ላይ ያለውን የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ጉዳይ የፈተሸበትን የዳሰሳ ጥናት አድርጓል:: በዚህ የዳሰሳ ጥናት መሰረትም በተለይ በተቋማት ለሚታዩ የአሰራር ችግሮችና የሙስና ጉዳዮች መበራከት አቅም የሆኑ "ምስለ ተገልጋይ" ግለሰቦች በእጅጉ መበራከታቸውን መለየት ችሏል::

ይሄ ደግሞ ዜጎች በተቋማት አገልግሎትን ፈልገው ሲሄዱ፣ አገልግሎት የሚያገኙት አገልግሎቱ ስለሚገባቸው ብቻ ሳይሆን፤ ለአገልግሎቱ በሚሰጡት ጉቦ ወይም እጅ መንሻ ልክ ስለመሆኑ፤ ለዚህም ጉዳይ የሚያሳልጡ ምስለ ተገልጋዮች ስለመኖራቸው ደርሶበታል:: እንደ ፓርቲም በዚህ ጉዳይ ላይ ከፍ ያለ ውይይት ተደርጎ ችግሮቹን ማረምና የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱን ማጥራት በሚያስችሉ አሰራሮች ላይ አቅጣጫ አስቀምጧል።

ይሄ ደግሞ ይበል የሚያሰኝ፣ ሀገርን ከሚመራ መንግስትና ፓርቲ የሚጠበቅ ተግባር ነው:: ምክንያቱም፣ እንደ ሀገር ቀደም ሲል የነበሩ ከፍ ያሉ (ግራንድ የሚባሉ) የሙስና ተግባራት ሀገርን ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈሉ ይታወቃል:: አሁን ላይ በዛ ልክ የሚጠቀስ የሙስና ተግባር አለ የሚል መረጃ ባይኖርም፤ በምስለ ተገልጋይ አንጻር እየተስፋፉ የመጡ ጥቃቅን የሙስና ልምምዶች እያደጉ መሄዳቸው፤ ድምር ውጤታቸውም የዜጎችን ምሬት ወልዶ ወደ ሌላ ችግር ማምራታቸው አይቀሬ መሆኑንም የተገነዘበም ነው::

ይሄ ጅምር ደግሞ ችግርን ከመለየት የተነሳ እንደመሆኑ፣ የችግሩን ሃምሳ በመቶ እንደመፍታት የሚቆጠር ይሆናል:: የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ማስቀመጡም ሌላ የችግሩ ማቃለያ አቅም ነው። ይሁን እንጂ ችግርን መለየት እና አቅጣጫ ማስቀመጥ ብቻውን ከችግር አያወጣም:: በጥናት የተለዩ ችግሮች ተለቅመው መፍትሄ እንዲያገኙ፣ በተግባር የሚገለጥ ርምጃ ያስፈልጋል::

ምክንያቱም ዛሬን በምስለ ተገልጋይ ገጽ ውስጥ የጀመረ የሙስና ልምምድ፣ ነገ ከፍ ወዳለው እና ሀገርን ዋጋ ወደሚያስከፍለው ትልቁ የሙስና እና የኮንትሮባንድ መስመር መግባቱ አይቀሬ ነው:: "ምነው በእንቁላሉ ጊዜ..." እንዲሉ፤ ከወዲሁ መሰል እንቅስቃሴና ተግባራትን መቅጨት ካልተቻለ፤ ዛሬ ላይ የዜጎችን እጅና ኪስ በመመልከት የተጀመረ ልምምድ፣ ነገ ከፍ ወዳለው የመንግሥት ካዝና ማማተሩና እጅ መስደዱ አይቀሬ ነው::

አሁን ላይ እየተነገራቸው የማይሰሙ፤ የሕዝብ ቅሬታና ብሶት የማያዳምጡ፤ የአገልጋይነት መንፈስን ሳይሆን የእጅ መንሻ ፍላጎትን ያዳበሩ፤... ኃላፊዎችና ባለሙያዎች እዚህም እዚያም መበራከት፤ ነገ የፓርቲውን ሕልውና በጥቅም የሚለውጡ ግለሰቦች ወደመሆን ላለመሸጋገራቸው ዋስትና አይኖርም:: በመሆኑም ብልፅግና እንደ መንግሥትም፣ እንደ ፓርቲም የጀመረውን ከፍ ያለ የለውጥ እና የብልፅግና ጉዞ፣ ጥቃቅን ጥላሸት ከሚያንኳኩበት ግለሰብና አንጃዎች ራሱን ሊያጠራ፤ በጥናት የለየውንም የመልካም አስተዳደር ችግር፤ የጥቃቅን ሙስናና ሙሰኝነት ልምምዶችን ከወዲሁ ፈር ሊያስይዝ ይገባዋል::

ይሄን ማድረግ ደግሞ የተጀመረውን እና ከፍ ብሎ እየተጓዘ ያለውን ሀገርን የማጽናት እና ለሁለንተናዊ ብልፅግና የማብቃት መንገድን እውን የማድረግ ብቻም ሳይሆን፤ ለሕዝብ የገቡትንም ቃል መፈጸም ነው:: ምክንያቱም፣ እንደ ፓርቲ ለመንግሥትነት በመወዳደር ሂደት ውስጥ ብልፅግና እንደ ፓርቲ አንዱ ለሕዝብ የተገባው ቃል፡-

"ፓርቲያችን የሕዝብ አስተዳደር ወይም ሲቪል ሰርቪስ ቅልጥፍናና ብቃት በየጊዜው እየጨመረ እንዲሄድ ያልተማከለ እና የተቋማቱን ባህሪያት ያገናዘበ፣ በጥናትና በእውቀት የሚመራ የለውጥ መርሃ ግብር በየተቋማቱ እንዲተገበር በማድረግ በመንግሥት ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ዜጎች ያላቸው እርካታና መተማመን እንዲጨምር በቁርጠኝነት እንሰራለን" የሚል ነው::

በመሆኑም እንደ መንግስት በየደረጃው ያለውን ሲቪል ሰርቪስ ወይም የሕዝብ አስተዳደር እየፈተሸ ማረም፤ በተለይም እንደ ፓርቲ በቅርቡ የተካሄደው የዳሰሳ ጥናት ያመላከታቸውን ዘርፈ ብዙ እና መልከ ብዙ የሙስና ተግባራት በእንጭጩ እንዲገቱ የማድረግ ቆራጥ ርምጃ መውሰድ ይኖርበታል:: በዚህም በልማትና ሌሎችም መስኮች የተገኙ ከፍ ያሉ ውጤቶች በላቀ መልኩ ሰው ተኮር ሆነው እንዲዘልቁና ለውጤት እንዲበቁ፤ ከፍ ያለ የሕዝብ እምነትና ተሳትፎዎችን እንዲያረጋግጡ ማድረግ ይቻላል:: ለዛሬው አበቃሁ፤ ሰላም!

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የነዳጅ መኪናውን ወደ ኤሌክትሪክ መኪና

ማህሌት አብዱል

በአርባዎቹ እድሜ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ጎልማሳ ነው፡፡ ውልደቱም ሆነ እድገቱ ወሊዲያ ከተማ ልዩ ስሙ መቻሬ በሚባል አካባቢ ነው፡፡ ከልጅነቱ ጀምሮ ለቴክኒክና ሙያ ነክ ነገሮች የተለየ ፍቅር ያለው በመሆኑ የሚያገኘውን ሁሉ ቁሳቁስ ፈቶ መልሶ መገጣጠም፤ የተሰበሩትን መጠገን ያስደስተውም ነበር፡፡

አቶ ዘመኑ ሲሳይ የሚባለው ይህ ጎልማሳ፣ በልጅነቱ ወላጆቹ የቀለም ትምህርት እንዲማር ትምህርት ቤት ቢልኩትም፣ እሱ ግን ምርጫው በአካባቢው ከሚገኙ የእንጨትና ብረታ ብረት ሥራ ከሚሰሩ ፋብሪካዎች ደጅ መዋል ነበር፡፡ ደብተሩን ይዞ ከማጥናት ይልቅም ከፋብሪካዎቹ እንጨት ለምኖ ከራርና መሰል ቁሳቁስን መስራት ያዘወትር እንደነበር ይናገራል፡፡

ይህ ፅኑ ፍላጎቱ አድጎ ገና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ ሳለ በሳምንት ለተወሰኑ ሰዓታት በእንጨት ቤቶቹ ተቀጥሮ በመስራት አስር ብር ያገኝም ጀመር። በወላጆቹ ጫና እስከ ሰባተኛ ክፍል ቢደርስም የትምህርት ውጤቱ ዝቅተኛ በመሆኑ ‘አካባቢ ሲቀይር ይለወጣል’ በሚል ተስፋ የእናቱ ቤተሰቦች ካሉበት ከሚሴ ከተማ ተላከ፡፡

እዚያም ቢሆን በትምህርቱ መበርታት አልቻለም፤ እንደ ምንም ስምንተኛ ክፍልን ለማጠናቀቅ ቢሞክርም ለትምህርት ፍላጎት ስላልነበረው ጠንክሮ ስላልተማረም የስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ማለፍ አልቻለም፡፡ የያኔው ታዳጊ የአሁኑ ጎልማሳ ዘመኑ ግን በፈተና መውደቁ ግድ አልሰጠውም፡፡

ስለትምህርቱ ከማሰብ ይልቅ ከአንድ እንጨት ፋብሪካ ተቀጠረና በሳምንት 40 ብር ማግኘት ጀመረ፤ ሙያውን በደንብ መልመድ ሲችል ወደ ወልዲያ ተመልሶ የራሱን የእንጨት ቤት ከፈተ፡፡ በክራር እጁን ያፍታታው አቶ ዘመኑ የተለያዩ የቤት ውስጥ ቁሳቁስን በመስራት በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት አገኘ፡፡ ለዚህም ሥራው የሚረዱትን እንደ መላጊያና መሰነጣጠቂያ ያሉ ማሽኖችን ፍለጋ ማንንም መለመን አላስፈለገውም፤ ይልቁንም እነዚህኑ ማሽኖች በራሱ እጅ አስመስሎ ሰራ። ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሚያያቸውን መሳሪያዎች አስመስሎ የመስራት የተለየ ስጦታ ያለው አቶ ዘመኑ፤ በተለይም ከውጭ በውድ የሚመጡና ለሰዎች ችግር ፈቺ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ቁሳቁስ ሁሉ ያለምንም ስልጠናና ትምህርት በአንድ ጊዜ እይታ ብቻ በመስራትም ብዙዎችን ማስደነቅ የጀመረው ገና በለጋ እድሜው ነው፡፡

‹‹መስራት የሚፈልገውን አስቀድሜ በጥንቃቄ ስለማየውና ስለማጠናው ስሰራውም ብዙ ሳልቸገር አሳካዋለሁ›› ሲል በልበ ሙሉነት ይናገራል፡፡ የወዳደቁ ቁሳቁስን ብቻ በመጠቀም የተለያዩ መሳሪያዎችን የሰራው ይህ የፈጠራ ባለሙያ፤ ከሰራቸውም መካከል ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀስበትን ሳይክል፣ የተለያዩ የእንጨት ማሽኖች፣ የብረት መበየጃ፣ የሸንኩርት መፍጫ፣ የሊጥ ማቡኪያና የመሳሰሉት የቤት ውስጥ ቁሳቁስ ይጠቀሳሉ፡፡

ይሁንና በ1997 ዓ.ም ተካሂዶ ከነበረው ሃገር አቀፍ ምርጫ ጋር ተያይዞ በተፈጠረው አለመረጋጋት ምክንያት የእሱም ድርጅት ሆነ የብዙዎቹ ፋብሪካዎች የሥራ እንቅስቃሴ ተቀዘቀዘ፡፡ ሁኔታው ስላላማረውም ሁሉን ነገር ትቶ ቀየውን ለቆ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ያስባል፤ አስቦ ብቻ አልቀረም፡፡

አንድ ማለዳ ተነስቶ ባገኘው የሕዝብ ትንስፖርት ከአዲስ አበባ ከተማ ይከሰታል፡፡ የትውልድ ቀዬው ሳለ ዝናዋን የሰማላት አዲስ አበባ ግን እንዳሰበው እጇን ዘርግታ አልተቀበለችውም፤ እንደተመኘውም ማደሪያው ፎቅ ቤት ሳይሆን የኮልፌ ከረንቡላ ቤት በረንዳ ሆነ። ችግር በበዛ ቁጥር ብርታቱን በመጨመር የበለጠ በመስራት ያምን ስለነበር ለአዲስ አበባ የቀን ሐሩር ሌት ቁር አልተበገረም፡፡ ጥቂት ቀናት በረንዳ ቆይቶ የብዙሃኑን የኑሮ ዘይቤ ለመቃኘት ሞከረ፤ በኋላም ከሃገሩ ቋጥሯት ከመጣው 820 ብር ውስጥ በ120 ብር ቤት ተከራየ፤ ከታላቅ ወንድሙ ካገኘው የ2ሺ500 ብር ድጋፍ የራሱን ሥራ ለመስራት ወጠነ፡፡

‹‹በ300 ብር የመስሪያ ቦታ ተከራየሁና የዳቦ፣ የሽንኩርት ማሽኖችን እንዲሁም የእንጨትና የብረት በርና መስኮቶችን ሁሉ መስራት ጀመርኩ›› በማለት ያስታውሳል፡፡ ሁሉን መሞከር የሚወደው ዘመኑ ቃሊቲ አካባቢ በመምጣት ደግሞ ጎሚስታ ቤት ከፈተ፡፡ ይሁንና ከሚያገኘው በላይ ግብር እንዲከፍል በመጠየቁና ፍትሕ



ፎቶ- ሐዱሽ አብርሃ

አቶ ዘመኑ ሲሳይ በነዳጅ የሚሠራ መኪናውን በኤሌክትሪክ እንዲሠራ ማድረግ ችሏል ፣

በማጣቱ ጎሚስታ ቤቱን ለመዝጋት ተገደደ፡

በደረሱበት ተደራራቢ ችግሮችና የስነ ልቦና ጫና ምክንያት ከአንድ ዓመት በላይ ገዳም መቆየቱን ይናገራል። ከብዙ ፀሎት በኋላ አዲስ አበባ ተመልሶ ከያኔዋ ሴት ጓደኛው (የአሁኗ ባለቤቱ) ጋር በመሆን ምግብ ቤት ከፈተ፤ ሥራ መናቅ የማያውቀው ዘመኑ በምግብ ሥራም ሆነ በእንጀራ ጋገራ አይታማም፡፡

የትዳር አጋሩ ከሆነችው ጓደኛው ጋር በመሆን የከፈቷትን ምግብ ቤታቸውን በሁለት እግሯ ለማቆም ደፋ ቀና ማለቱን ተያያዘው፡፡ የቴክኒክ እውቀቱን በመጠቀም የሻይ ማሽን ሰራ፤ ይህንን ጊዜ የምግብ ቤቱም ገበያ እየደራ ደንበኞቹም እየተበራከቱለት መጡ፡፡ ግን ደግሞ ችግሩ በዚህ አላበቃም፤ ቤቱን ያከራዩት ግለሰብ ምግብ ቤቱን መልመዱን ሲመለከቱ ራሳቸው ሊሰሩበት አስበው አስለቋቋቸው፡፡

በዚህ ምክንያት ወደ ጎሚስታው ሥራ ተመልሶ ገባ። ብዙም ሳይቆይ መንግስት የሰጠውን እድል ተጠቅሞ ከሌሎች ሰዎች ተደራጅቶ የብረታ ብረት ሥራ ጀመሩ። ‹‹ግን አብረውኝ ተደራጅተው የነበሩ ሰዎች ቶሎ ገንዘብ ማግኘት የሚፈልጉ ስለነበሩ፤ ሥራው እንዳሰቡት ሳይሆን ሲቀር ተራ በተራ እየለቀቁ መጨረሻ ላይ ብቻዬን መስራት ቀጠልኩ›› ይላል፡፡ በተሰጠው የመስሪያ ቦታ የብሎኬት ማምረቻ ማሽን፣ ሸንኩርት መፍጫና የዳቦ ማቡኪያ ማሽኖችን ማምረት ቀጠለ፡፡ በዚህም አልተወሰነ፤ ብዙ አምራቾች የሚቸገሩበትን ነገር በማጤን ያገለገሉ ጀነሬተሮችን በማደስ በማከራየትና በመሸጥ ገቢውን ማሳደግ ቻለ።

ምንም እንኳ በቀለም ትምህርቱ ገፍቶ ባይሄድም ለአዳዲስ ነገሮችና ለፈጠራ ሥራዎች ልቡ ክፍት የሆነው ይህ የፈጠራ ባለሙያ፤ ወቅቱን ባገናዘቡና የሕዝብ ችግር ፈቺ በሆኑ ነገሮች ላይ ጥናት ማድረግ ይጀምራል፡፡ ሩቅ ሳይሄድም በየሳምንቱ ከአራት ሺ ብር ያላነሰ የነዳጅ ወጪ የምታስወጣውን ቮልስ ዋገን መኪናውን በምን መልኩ ወጪዋን ሊቀንስ እንደሚችል ማሰላሰል ቀጠለ። በሌላ በኩል መኪናዋ እድሜ ጠገብ በመሆኗ ወደፊት ከአገልግሎት ውጪ የምትሆንበት አጋጣሚ ሊፈጠር ስለሚችል ሁለቱንም ችግሮች መፍታት ያስችለው ዘንድ ወደ ኤሌክትሪክ መኪናነት ለመቀየር አለመ፤ አልሞ ብቻ አልቀረም፤ ሕልሙን እውን ማድረግ ቻለ፡፡

‹‹መጀመሪያ የተለመደውን የመኪና ባትሪ አድርጌ፤ ሞተርና ሌሎችንም አስፈላጊ ቁሳቁስ ከሰዎች ላይ ገዛሁና ገጣጥሜላት ስሞክራት የተወሰነ ርቀት ተጉዛ ቆመች፤ ይህም የሆነው የተጠቀምኩት ሊድ አሲድ ባትሪ ስለነበርና እንዲህ አይነቱ ባትሪ ደግሞ ጥቅም ላይ የሚውለው ለመንደርደሪያ ብቻ ስለነበር ነው›› በማለት የመጀመሪያ ሙከራውን ያስረዳል፡፡

ይህ ሁኔታም ተስፋ አላስቆረጠውም፤ በሁለተኛው ሙከራውም ሌላ አይነት ባትሪ ቀይሮ ያለነዳጅ ሞከራት፤ አሁንም ካለፈው በተሻለ ጥቂት ተጉዛ ቆመች፡፡ ይህን የአቶ ዘመኑን የቀን ተቀን ሙከራ ያዩ አንዳንድ ሰዎች የማሾፍና ተስፋ የሚያስቆርጡ አስተያየቶች ይሰነዝሩበት እንደነበር ያስታውሳል፡፡

በዚህም አልተበገረም፤ ካሰበበት ለመድረስ ሌት ተቀን መትጋቱን ቀጠለ፤ አንድ የኤሌክትሪክ ባለሙያ አማከረና ረጅም ጊዜ ሊቆይ የሚችል ባትሪ ገዝቶ ገጠመለት፤ እንደተመኘውም ሳሪስ ከሚገኘው የመስሪያ ቦታው አቃቂ ወደሚገኘው ቤቱ ደርሶ መመለስ ቻለ፡፡ ይህም ይበልጥ ሞራል ሰጠው፤ በየቀኑ ቻርጅ እያደረገ ከቤት መስሪያ ቤት፣ ከመስሪያ ቤት ወደ ቤት መመላለሱን ቀጠለ፡፡

ከዚህ የተሻለ ረጅም ጊዜ የሚቆይ ‘ሌቲየም’ የተባለ ባትሪ እንዳለ ሰዎች ቢጠቁሙትም ዋጋው የሚቀመስ አልሆነለትም፡፡ በመሆኑም በእጁ ያለው ባትሪ ራሱን በራሱ ቻርጅ የሚያደርግበትን ስርዓት ፈጠረ፡፡ በአዲስ መልክ ሞተሯ በኤሌክትሪክ እንዲሰራ ተደርጎ የተቀየረላት የአቶ አመኑ ቮልስ መኪና አሁን ባለችበት ሁኔታ ሁለት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ቻርጅ በማድረግ እስከ 120 ኪሎ ሜትር መጓዝ ትችላለች፡፡ ዘመን አሁንም መጠበቡን አላቆመም፡፡ የበለጠ ለማሻሻልና ለማዘመን ቀን ሌት ተሌት እየተጠበበባት ነው፡፡ በዚህም ሞተር ወይም ዲናሞን ጨምሮ 80 በመቶ የሚሆነውን የመኪናውን ክፍል በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

የነዳጅ ተሽከርካሪን ወደ ኤሌክትሪክ መቀየር የቻለው ይኸው የፈጠራ ሰው ለሃገሩ ባመጣው አዲስ ግኝት በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ላይ በሚዘጋጀው ነጋድራስ በተሰኘው የሥራ ፈጠራ ውድድር ላይ አሸንፎ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር ተሸላሚ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም 10 ሚሊዮን ብር ያለምንም ኮላተራል መበደር የሚችልበት እድል ተመቻችቶለታል፡፡

ይህ የፈጠራ ሰው ከዘጠኝ ወር አድካሚ ምልልስ በኋላ የኢትዮጵያ አዕምራዊ ንብረትም የባለቤትነት እውቅናም (ፓተንት ራይት) አግኝቷል፡፡ ይህንን ድንቅ የፈጠራ ሥራ የተመለከቱ 12 ሺ የሚልቁ ሰዎች መኪናቸውን ወደ ኤሌትሪክ እንዲቀይርላቸው ጥያቄ እንዳቀረቡለትም ይናገራል፡፡

ይህን ጥያቄ ለመመለስም ሆነ አገልግሎት ላይ ለማዋል ግን በቅድሚያ የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ፈቃድ ያስፈልገዋል፡፡ ለእዚህም ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረቡን ጠቅሶ፣ ይሁንና ላለፉት አምስት ወራት ምንም አይነት ምላሽ አለማግኘቱን ነግሮናል፡፡

‹‹ፈቃዱ የሚያስፈልገው ይህች እኔ ወደ ኤሌክትሪክ መኪና የቀየርኳት ቮልስ ዋገን መኪና የምትታወቀው በነዳጅ በመሆኑና አሁን ያለችበትን ሁኔታ የሚያሳይ ፈቃድ ከሚኒስቴሩ ሊሰጣት ስለሚገባ ነው፤ ለዚህም ሰኔ 26 ቀን 2016 ዓ.ም ማመልከቻ አስገብቻለሁ፤ እስካሁን ግን ምንም አይነት ምላሽ አላገኘሁም›› ይላል፡፡

አሁንድ ሰዎች እዚህ ሁሉ ደረጃ ላይ ደርሶም ሥራውን ለማመን እንዳልፈለጉ ጠቅሶ፣ ጥቂቶቹም እንደሚሳለቁ ይናገራል፡፡ ‹‹ቮልስ መኪናዬ ላይ ‘የኤሌክትሪክ መኪና’ መሆኗን የሚገልጽ ፅሁፍ አድርጌያለሁ›› ሲል ገልጾ፣ ይህን የተመለከቱ አንዳንዶች ‘ምኞት ነው’ እያሉ እንደሚሳለቁበትም ይገልጻል፡፡ ‹‹ሌሎችም አስቁመውኝ ፈትሸን ካላየን ብለው የሚሟገቱኝ አሉ›› ሲል ጠቅሶ፣ ‹‹ይህ ሁኔታ እንዲህ አይነቱን ቴክኖሎጂ የውጭ ዜጋ ካልሰራው አልያም ከውጭ ካልመጣ ለመቀበል የሚቸገሩ እንዳሉ ያመለክታል›› ብሏል፡፡

ይህም የራስን ሃብት ካለማወቅና ማክበር ካለመፈለግ እንደሚነጭ አስታውቆ፣ እንዲህ አይነቱ ንግግር የፈጠራ ባለሙያዎችን ተስፋ ሊያስቆርጥና ወደ ኋላ ሊጎትት እንደሚችልም አመልክቷል፡፡ ‹‹ እኔ ማንም ምንም ቢለኝ ግድ የለኝም፤ እየሰራሁ ነው፤ አሁን ሙከራዬን ጨርሼ 12 ሺ 700 ሰዎች መኪናቸውን ወደ ኤሌትሪክ እንዲቀይርላቸው ጠይቀውኛል፤ ለዚህም የሚሆነኝን ቦታ አዘጋጅቻለሁ፤ የምጠብቀው የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴርን ይሁንታ ብቻ ነው›› ሲልም አስታውቋል፡፡

እሱ እንዳለው፤ ከዚህ ቀደም ለመኪናዋ የነዳጅ በሳምንት አራት ሺ ብር፤ በዓመት ደግሞ ከ180 ሺ ብር በላይ ያወጣ ነበር፤ ወደ ኤሌትሪክ ከቀየራት ወዲህ ግን 120 ኪሎ ሜትር (ለሁለት ቀናት) ተጉዞ 16 ብር ብቻ ነው ወጪ የሚያደርገው፡፡ በሳምንት ሶስት ጊዜ ቻርጅ ካደረጋት ደግሞ በ40 ብር እንዳሻው መጠቀም ይችላል።

በሌላ በኩል ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ተገዝተው የሚመጡት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ባትሪዎች አንድ ላይ ተያይዘው የተሰሩ በመሆናቸው ችግር ሲደርስባቸውም ሆነ አቅማቸው ሲዳከም ጉዳት የሚደርስባቸው አንድ ላይ መሆኑን ያስረዳል። የእሱ የፈጠራ ውጤት የሆነችው የኤሌክትሪክ መኪና ግን አምስት ባትሪዎች ያሏትና በተናጠል የተገጠሙ ናቸው፡፡ ይህ መሆኑም የአንዱ ኃይል ሲያልቅ ከሌላኛው እየወሰደ (እርስ በርስ ቻርጅ እየተደራረጉ) ረጅም መንገድ መጓዝ የሚያስችል ነው፡፡ ይህም ከአላስፈላጊ ወጪ የሚታደግ በመሆኑና ባልተወሳሰበ ግብዓት የተሰራ መሆኑ የተለየ ያደርገዋል ባይ ነው፡፡

ይህችን መኪና መጀመሪያ ሲሰራ ለነዳጅ የሚያወጣውን ገንዘብ ለማዳን ነበር፤ አሁን ደግሞ እንደ መንግስትም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ መጠቀም ፋይዳው ብዙ ነው፡፡ ሃገር ለነዳጅና ለመለዋወጫ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ የሚታደግ በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቼ እየሰራሁ ነው ሲልም ያብራራል፡፡

አቶ ዘመኑ ይህን የፈጠራ ሥራውን በአሁኑ ወቅት በሚኒባስና የብዙሃን ትራንስፖርት በሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ላይ ሙከራ እያደረገ ይገኛል፡፡ ይህም የሕዝቡን የትራንስፖርት ችግር ለመፍታት እንደሚያስችል ያስረዳል፡፡ ‹‹በቀጣይም ለመኪኖቹ የራሳቸውን ቻርጀር አብሮ የመግጠም እቅድ አለኝ›› ይላል፡፡

በተጨማሪም አዳዲስ መኪናዎችንም ለመስራት ዝግጅት እያደረገ መሆኑን፤ ለናሙና ያህልም አንድ መኪና በመስራት ላይ እንደሆነ ይጠቁማል። ‹‹ሁሉንም ነገር ከውጭ ከምናመጣ የተወሰኑትን አምጥተን ሌላውን በራሳችን አቅም እዚሁ ሃገራችን ውስጥ መስራት መቻል አለብን›› ሲል ይጠቁማል። ከዚህ ባሻገርም ያገለገሉና ከጥቅም ውጪ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን በመጠገንና ወደ ኤሌክትሪክ በመቀየር ሃገሪቱ በዘርፉ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ መታደግ፤ የአየር ብክለትን መቀነስ ብሎም ለበርካቶች የስራ እድል መፍጠርን ያነገበ ዓላማ ይዞ እየሰራ ይገኛል፡፡

‹‹እኔ ብቻዬን መስራት አልፈልግም፤ ይህ ሥራ ሰፊና ብዙዎችን የሚያሳትፍ ትልቅ ኢንዱስትሪ ነው፤ የትንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴርን ይሁንታ አግኘቼ ሥራውን ከጀመርኩኝ፤ የመኪናው የተለያዩ ክፍሎች በሌሎች አካላት እንዲመረቱ በኮንትራት የሚሰሩበትን ሁኔታ አመቻቻለሁ›› ሲልም ጠቁሟል፡፡ እስካሁን ለ11 ወጣቶች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል መፍጠሩን ገልጾ፣ ወደፊት ግን ከ350 የሚልቁ ዜጎችን የሥራ እድሉ ተጠቃሚ ለማድረግም እቅድ መያዙንም አስታውቋል፡፡

‹‹በሃገራችን የፈጠራ ሥራን የማበረታታት ባህል እምብዛም አልነበረም›› የሚለው አቶ ዘመኑ አሁን ላይ በተለይ የፋይናንስ ተቋማት አዲስ የፈጠራና የሥራ ሃሳብ ላላቸው ዜጎች ያለምንም ኮላተራል ብድር ማግኘት የሚችሉበት እድል ማመቻቸታቸው እንደሱ ላሉ የፈጠራ ባለሙያዎች ተስፋ የሚሰጥና የበለጠ ለመስራት የሚያሳሳ እንደሆነ ይናገራል፡፡

በሽልማቱ ያገኘውን ገንዘብና ከባንክም ብድር በመጠየቅ ድርጅቱን የማስፋት እቅድ ይዞ እየሰራ መሆኑን ጠቅሶ፣ ለዚህም ይረዳው ዘንድ በአሁኑ ወቅት ስድስት ሺ ካሬ የሚሆን የመስሪያ ቦታ ተከራይቶ የሥራ ፈቃዱን እየተጠባበቀ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ታታሪው ይህ የፈጠራ ባለሙያ የፈጠራ ውጤቱ ለሃገር የሚያበረክተውን በጎ አስተዋፅኦ በመረዳት ትራንስፖርና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴርም ሆነ ሌሎች መንግስታዊ ተቋማት ትብብራቸውን እንዲያቀላጥፉለት መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡

# ወቅታዊ ትንታኔ

# በቅሬታ አቀራረብ መስተንግዶ ላይ የሚታዩ ክፍተቶች እንዴት እየታረሙ ነው?

**አመለወርቅ ከበደ**

የአስተዳደር ሕግ የመንግሥት አስተዳደር ተቋማት ለዜጎች የሚሰጡትን አገልግሎት በፍታዊነትና የሕግ የበላይነትን ባከበረ መልኩ እንዲሰጡ ለማስቻል በአዋጅ ቁጥር 1183/12 ጸድቆ በሥራ ላይ ከዋለ የተያዘውን ዓመት ሳይጨምር አራት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በእነዚህ ዓመታት 30 የመንግሥት አስተዳደር ተቋማት ላይ ክትትል ተደርጓል፡፡

አዋጁ በዋናነት የተቋማት መመሪያ አወጣጥና እና አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ትኩረቱን የሚያደርግ ሲሆን፤ ሰሞኑን በ2014 ዓ.ም ክትትል በማድረግ ምክረሀሳብ የተሰጣቸው ሰባት ተቋማት ላይ ዳግም ክትትል ተደርጎባቸው የተሰጠውን ምክረሀሳብ ምን ያክል እንደፈጸሙ የሚያሳይ የግምገማ ሪፖርት በፍትህ ሚኒስቴር በኩል ይፋ ተደርጓል፡፡

ክትትሉ የተደረገባቸው የመንግሥት ተቋማት ገንዘብ ሚኒስቴር፥ ትምህርት ሚኒስቴር፥ ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር፣ ጤና ሚኒስቴር፥ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ገቢዎች ሚኒስቴር እና ጉምሩክ ኮሚሽን ናቸው፡፡

በወቅቱ የፍትህ ሚኒስትር ወይዘሮ ሐና አርአያስላሴ እንደገለጹት፤ ብዙ ግዜ ስለፍትህ ሲታሰብ የፍትሐብሄር እና የወንጀል ሕጎች ይታሰባሉ፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ ሰዎች ከመንግስት አስተዳደር ተቋማት ጋር ባላቸው ግንኙነት አካታች የሆነ የሕግ ሥርዓት መኖሩ ለፍትህ መረጋገጥ ፋይዳ ያለው ነው፡፡

ከዚህ አንጻር የመንግሥት አስተዳደር ሕግ፤ ተቋማት በእኩልነት፣ ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ስልጣንና ተግባራቸውን እንዲያስፈጽሙ የሚያስችል የሕግ ማሕቀፍ ነው፡፡ በመሆኑም እንደ አንድ ሕዝባዊ የመንግሥት አስተዳደር የፍትህን ማስፈን ተገቢነት በመገንዛብ የአስተዳደር ሕግ አዋጅ በ2012 ዓ.ም ጸድቆ ወደ ሥራ መግባቱን አብራርተዋል።

ቀድመው በተሰሩ የክትትል ሥራዎች የተገኙ ግኝቶች የተቋማትን ጠንካራ እና ደካማ ጎን አጉልቶ ማሳየት ብቻ ሳይሆን ተቋማት ለአስተዳዳር ፍትህ እና ለሕግ የበላይነት መስፈን ላላቸው ቁርጠኝነት ትልቅ ዓላማ ያለው መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

በተሰራው ግምገማ ከዚህ በፊት ከነበረው ግብረ መልስ በኋላ ብዙ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡ ተቋማት በመመሪያ አወጣጥ ሂደት ላይ የነበረባቸውን ክፍተት ፈተው፤ ሂደቱን በጠበቀ መልኩ ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግ ላይ ብዙ የተሻሻሉ ነገሮች አሉ፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ውስንነቶች ታይተዋል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የሕጎች ተፈጻሚነትን መከታተል አንዱ የፍትህ ሚኒስቴር ተግባር እንደመሆኑ፤ በቀጣይ እነዚህ ተቋማት ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተቋማትን በማካተት የአስተዳደር ሕጉ ምን ያህል እየተፈጸመ ነው የሚለው በቋሚነት የሚታይ ይሆናል ሲሉ ይጠቁማሉ፡፡

የተገኘውን የአፈጻጸም ግምገማ ውጤት የመንግሥት አስተዳደር ተቋማት ለመልካም አስተዳደር ቁርጠኝነት እንዲያውሉት ሲሉ ምክረ ሀሳባቸውን ያቀርባሉ፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግና የፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ አቶ ኢፋ ቦሩ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ አዋጁ የተዘጋጀበት ዓላማ እውን እንዲሆን እና እንዲሳካ አስፈጻሚ የመንግሥት አካላት ለአዋጁ ተገዢ በመሆን በተሟላ ሁኔታ እንዲፈጽሙት ይጠበቃል፡፡

የአዋጁን አፈጻጸም በተመለከተ በተለያዩ ተቋማት የመጀመሪያና ዳግም ክትትል በማድረግ የውይይት መድረኮች በማዘጋጀት ምክረሀሳቦች ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ ይፋ የተደረገው ሪፖርትም የዚህ አንድ አካል ሲሆን፤ ውጤቱ ተቋማት በላቀ አፈጻጸማቸው እውቅና እንዲያገኙ እና ክፍተት ባሳዩት ተግባር ተጠያቂ ኢንዲሆኑ የሚያስችል ነው ይላሉ፡፡

የአዋጁ አፈጻጸም በመንግሥት ቁርጠኛ አቋም የተወሰደበት መሆኑ ታውቆ፤ የመንግሥት አስተዳደር ተቋማት በአዋጁ መሰረት ቁርጠኛ አመራር ሊሰጡና ተገቢ ክትትል ሊያደርጉ እንደሚገባ ያሳስባሉ፡፡

**የመንግሥት አስተዳደር ሕግ፤ ተቋማት በእኩልነት፣ ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ስልጣንና ተግባራቸውን እንዲ ያስፈጽሙ የሚያስችል የሕግ ማሕቀፍ ነው። በመሆኑም እንደ አንድ ሕዝባዊ የመንግሥት አስተዳደር የፍትህን ማስፈን ተገቢነት በመገንዛብ የአስተዳደር ሕግ አዋጅ በ2012 ዓ.ም ጸድቆ ወደ ሥራ ገብቷል**

በፍትህ ሚኒስቴር የፌደራል ሕጎች ተፈጻሚነት መከታተል ዳይሬክተር ሀወኒ ታደሰ እንደገለጹት፤ ተቋማት ላይ ክትትል ሲደረግ የሕግ ዳሰሳ፣ቃለመጠይቅ፣ የመስክ ምልከታ እና የሪርፖቶች ዳሰሳ ተደርጓል፡፡ ናሙና አወሳሰድ በተመለከተ በተቋማቱ ጉዳይ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ቃለመጠይቅ ተደርጓል፡፡

የአስተዳደር ውሳኔ እና ቅሬታ አፈታትን በተመለከተ ዘፈቀዳዊ በሆነ መልኩ መረጃ ለመውሰድ ተችሏል፡፡ የተገኘው መረጃ ከሕጉ ጋር እና ቀድሞ ከተሰጡት ምክረሀሳቦች በማገናዘብ መተንተኑን ያስረዳሉ፡፡

የመመሪያ አወጣጥና ሕጋዊ ሂደት በተመለከተ ገንዘብ ሚኒስቴር ከ2014 ዓ.ም በኋላ ለተዘጋጁ ሁሉም አዋጆች መስሪያ ቤቱ የጽሁፍ ማብራሪያ ማዘጋጀት መቻሉ እና ለሚመለከታቸው አካላት ለአስተያየት መላኩ እንደጥንካሬ መወሰዱን ይናገራሉ፡፡

የመጀመሪያው ክትትል ከተደረገ በኋላ መስሪያ ቤቱ ስምንት አዳዲስ መመሪያዎችን በሥራ ላይ አውሏል፡፡ መመሪያዎቹን አይቶ ማንኛውም ሰው አስተያየት መስጠት እንዲቻል ጋዜጣ ላይ ማስታወቂያ ማውጣት ተገቢ መሆኑ ቢቀመጥም መስሪያ ቤቱ ይህን አለማድረጉን ይገልጻሉ፡፡

ሌላው ተቋሙ ለስምንቱም መመሪያዎች መዝገብ አለማደራጀቱ፣ አሳታፊ የውይይት መድረክ አለማዘጋጀት፣ ሁለት መመሪያዎች ስልጣን ሰጪ ሕግ ሳይኖር መውጣታቸው እና ነባር አዋጆችን አለማስመዝገብ በክትትሉ የታየ ክፍተት መሆኑን ያነሳሉ፡፡

ዳይሬክተሯ እንደሚሉት በትምህርት ሚኒስቴር በኩል በዳግም ክትትሉ ግዜ የወጡ መመሪያዎች በስልጣን ሰጪ አካል ስልጣን የሚሰጣቸው ሕግ መኖሩ ተረጋግጦ መውጣቱ እና አዲስ መመሪያ የማስመዝገብ ሂደቱ የሚደነቅ ነው፡፡ ነገር ግን በቅድመ መመሪያ አወጣጥ ግዜ የተቀመጡ ስርዓቶች አለመሟላታቸውን አብራርተዋል፡፡

በባለድርሻ አካላት ለሚሰጡ አስተያየቶች ተቋሙ ማብራሪያ አላዘጋጀም፡፡ በተጨማሪም በረቂቅ ደረጃ በቀረበው መመሪያ እና በጸደቀው መመሪያ መካከል ስላለው ልዩነት የጽሁፍ ማብራሪያ አለማዘጋጀት፣ መመሪያዎቹን በሁለት ቋንቋ አለመዘጋጀት እና ነባር መመሪያዎች በተቋሙ ድረገጽ ላይ አለመጫናቸው እንደ ክፍተት መታየታቸውን ያስረዳሉ፡፡

ሀወኒ እንደሚሉት፤ ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በኩል እንደጥንካሬ የተወሰደው፤ መመሪያን በተሰጠ ስልጣን ስር ማውጣት፣ ለፍትህ ሚኒስቴር እና ለሚመለከታቸው አካላት ለአስተያየት ማቅረብ፣ አስተያየቶችን በጽሁፍ መቀበል እና ማብራሪያዎችን ማዘጋጀት ነው፡፡

መመሪያ ከመውጣቱ በፊት መደረግ የነበረባቸው አንዳንድ ስርዓቶች አለመደረጋቸው እንዳለ ሆኖ፤ በንግድ ሕጉ መሰረት አንድ ሰው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚያቋቁምበትን ስርዓት የሚደነግግ መመሪያ ማዘጋጀት በአስገዳጅነት መቀመጡን ያነሳሉ።

ነገር ግን በተቀመጠው የሶስት ወር የግዜ ገደብ ውስጥ መመሪያው ሳይወጣ መቅረቱ ዜጎች ለሚያቀርቡት ጥያቄ አገልግሎት ላለመስጠት ምክንያት መሆኑ እና መመሪያዎችን በተቋሙ ድረገጽ ተደራሽ አለማድረግ እንደ ድክምት መታየቱን ያስረዳሉ፡፡

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በዳግም ክትትል ግዜ ውስጥ ምንም አይነት መመሪያ አላወጣም፡፡ ነገር ግን አንድ የአሰራር ስርዓት ሰነድተገኝቷል፡፡ የአስተዳደር ስርዓት አዋጁ ሰነዶች ከሚሰየሙት ስያሜ ጋር ጉዳይ የለውም፡፡

ስለዚህ የትኛውም ለአሰራር ስርዓት የተዘጋጀ መመሪያ በተገልጋዩ ዘንድ ውጤት ካመጣ እንደመመሪያ እንደሚቆጠር እና የመመሪያን ቅድመ ስርዓት ተከትሎ መውጣት እንዳለባቸው አዋጁ ይደነግጋል፡፡ ተቋሙ በተገልጋዮች መብትና ጥቅም ላይ በመመሪያ ደረጃ ባልወጣ ሰነድ መወሰኑ እንደክፍተት ተወስዷል ይላሉ፡፡

ገቢዎች ሚኒስቴር በክትትል ግዜ ውስጥ አምስት መመሪያዎችን ያወጣ ሲሆን፤ ለፍትህ ሚኒስቴር ለአስተያየት መላካቸው፣ በሶስቱ መመሪያ ላይ የማብራሪያ ጽሁፍ መዘጋጀቱ እና አብዛኞቹ መመሪያዎች ከመመሪያ ቅርጽና ይዘት አንጻር የተሟሉ መሆናቸው በጥንካሬ መወሰዱን ይናገራሉ፡፡

መዝገብ አለማደረጀት፣ ማስታወቂያ በድረ ገጽ ወይም በጋዜጣ አለማውጣት፣ ማንኛውም አካል ሊሳተፍበት የሚችል የውይይት መድረክ አለማዘጋጀት፣ ለባለድርሻ አካላት ረቂቁን ለአስተያየት አለመላክ እና የመመሪያዎችን ቅጂ በእንግሊዘኛ ቋናቋ አለማዘጋጀት በደካማ ጎን ተወስዷል ይላሉ፡፡

ሀወኒ እንደሚሉት፤ ጤና ሚኒስቴር በክትትል ግዚያት ውስጥ ያጸደቀው መመሪያ ባይኖርም፤ አራት እረቂቅ መመሪያዎችን አዘጋጅቷል፡፡ ስለዚህ ክትትሉ የሚደረገው ረቂቁ እስከደረሰበት ደረጃ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር በረቂቅ መመሪያዎቹ ላይ በድረገጽ አስተያየት መስጠት እንደሚቻል መታወጁ እንደ ጥንካሬ ተወስዷል፡፡ እስካሁንም ባለው ሂደት መመሪያዎቹ ተገቢውን ይዘው ቀጥለዋል፡፡ መዝገብ አለማዘጃት፣ በጋዜጣ ማስታወቂያ አለማውጣት፣ ለባለድርሻ አካላት አለመላኩ እና የሕዝብ ውይይት አለማድረግ እንደክፍተት ይጠቅሳሉ፡፡

ሌላኛው በአዋጁ ላይ የተቀመጠው፤ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጭነትን እና ሕጋዊ አፈጻጸምን በተመለከተ ነው፡፡ የኢፌዴሪ ገንዘብ ሚኒስቴር አስተዳደራዊ ውሳኔ ጥያቄን በአካልና በኤሌክትሮኒክስ መንገድ በጽሁፍ ሊቀርብ የሚችልበትን መንገድ ዘርግቷል፡፡ እንዲሁም የሚቀርቡ አቤቱታዎችን የሚሰማበት አግባብ መኖሩ እንደጥንካሬ መታየቱን ይገልጻሉ፡፡

ዳይሬክተሯ እንደሚሉት፤ በተቋሙ ቅሬታ ማስተናገጃ መቋቋሙ የሚደነቅ ቢሆንም፤ በቂ በሆነ በሰው ኃይል ያልተደራጀ መሆኑ እንደውስንነት ታይቷል፡፡ አንድ ሰው አቤቱታ ሲያቀርብ አቤቱታ እንዳቀረብ ማረጋገጫ ሊሰጠው የሚገባ ቢሆንም ገንዘብ ሚኒስቴርን ጨምሮ ስድስቱም መስሪያ ቤቶች ይህን አላደረጉም፡፡

ዜጎች አቤቱታ ሲያቀርቡ ተቋሙ አቤቱታውን መቀበሉ የሚያረጋግጥ ማብራሪያ መስጠቱ ብዙ ምልከታ አለው፡፡ ቅሬታ አቅራቢው በወቅቱ ውሳኔ አልተሰጠኝም ቢል እንኳን እንደግዜ ማጠቀሻነት ለማቅረብ ያግዛል፤ ተቋማት በግዜ ገደብ ውስጥ ሥራቸውን እየሰሩ ነው የሚለውን ለመለካት ያግዛል ይላሉ፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ ትምህርት ሚኒስቴር ጥያቄዎችን በጽሁፍ፣ በኦንላይን እና በአካል የሚቀርብበትን አሰራር ዘርግቷል፤ ዜጎች የሚያቀርቡትን ማስረጃ የመመርመር እና ውሳኔ የመስጠት ሥራዎችን ሲሰጥ እንደጥንካሬ ተወስዷል። ውሳኔ ሲሰጥ ዋናው ፍሬ ነገሩ ምንድነው የሚለው ተተንትኖ እንዲቀርብ አዋጁ ይደነግጋል፡፡

ነገር ግን በተቋሙ የሚሰጡ ውሳኔዎች ትንተና የማይካሄድባቸው መሆኑ፣ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል እስካሁን አለመቋቋሙ እንደድክመት መወሰዱን ያስረዳሉ፡፡

ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አቤቱታ የመቀበል እና ውሳኔ አሰጣጥን ዲጂታላይዝድ ከማድረግ አንጻር፣ ውሳኔዎች ገላጭ በሆነ መልኩ በጽሁፍ መሰጠታቸው፤ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት አግባብነት ያለው ማስረጃን ከአቤቱታ አቅራቢዎች መስማቱ በጥንካሬ ታይቷል፡፡ አልፎ አልፎ ቅሬታዎች በቃል መቅረባቸው እና የተቋሙ ቅሬታ ሰሚ አካል የውሳኔ ሀሳቦችን ለመስሪያ ቤቱ የበላይ አካል አለማቅረቡ በድክመት መወሰዱን ይገልጻሉ፡፡

ሀወኒ እንደሚናገሩት፤ ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የቅሬታ ሰሚ አካል አቋቁሟል፤ ጉዳዩን በአግባብ ሰምቶ ውሳኔ መስጠት እና አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዴት እንደሚሰጥ ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር በመሆን ለሰራተኞች ስልጠና መስጠቱ በጥንካሬ ተወስዷል፡፡

ማረጋገጫ አለመስጠት፣ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎችን በጽሁፍ አለማሳወቅ፣የተሟላ ይዘት ያለው አስተዳደራዊ ውሳኔ አለመስጠት እና ቅሬታ ሰሚው ክፍል በተሟላ ባለሙያ አለማደራጀት እንደክፍተት ታይቷል ይላሉ፡፡

ገቢዎች ሚኒስቴር ቅሬታ አሰማም ስርዓት በተመለከተ በአዋጅ የተቀመጠ መመሪያ አለው፡፡ በዚህ አብዛኛው ቅሬታ የሚሰማበት አካሄድ የአስተዳደር አዋጁን ባከበረ መልኩ በመሆኑ ከአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ አንጻር መስሪያቤቱ የላቀ ውጤት አስመዝግቧል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ከድክመት አንጻር አሁንም በስልክና በቃል ቅሬታ እንዲቀርብ የሚፈቅድ መመሪያ መኖሩ ከ1183 አዋጅ ጋር የሚጣጣም አይደለም፡፡ አቤቱታ አጣሪ ጽህፈት ቤት ለማቋቋም ከወጣው መመሪያ አንጻር ተገቢውን የሙያ ስብጥር አለማሟላት እና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተገቢውን ሕግ አለመጥቀስ እንደ ክፍተት ተወስዷል ይላሉ፡፡

ከጤና ሚኒስቴር አንጻር አቤቱታዎችን በኤሌክትሮኒክስ እና በአካል ማቅረብ መቻል፤ በቃል የሚቀርቡ አቤቱታዎች እንዲቀሩ መደረጉ በጥንካሬ ታይቷል፡፡ የተቋሙ የቅሬታ ሰሚ አካል የተቋቋመ ቢሆንም፤ መቋቋሙ ለሕዝብ ግልጽ አለመደረጉ በክፍተት የታየ መሆኑን ያነሳሉ፡፡

በክትትሉ ጉምሩክ ኮሚሽን ግምገማ የተደረገበት በአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ብቻ ነው፡፡ ጉምሩክ ኮሚሽን ቀድሞ የተሰጠውን የማስተካከያ ምክረሀሳብ አብዛኛውን ለመፈጸም ችሏል፡፡ ተቋሙ አቤቱታዎችን ሆነ ሌሎች ወደ ተቋሙ የሚላኩ ሰነዶች በኦንላይን እንዲላክ ማድረጉ፣ ዜጎች ያላቸውን አቤቱታ በአማርኛም በእንግሊዘኛ ቋንቋ እንዲልኩና ከላኩም በኋላ የመከታተያ መለያ ቁጥር መሰጠቱ በጥንካሬ ተወስዷል ይላሉ፡፡

ከድክመት አንጻር በጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የቅሬታ አጣሪ ሥራ ክፍል መኖሩን የሚያነሱት ዳይሬክተሯ፤ የሥራ ክፍሉን አሰራር ለመወሰን የወጣ መመሪያ የአባላት ስብጥር ምን መሆን እንዳለበት አዋጁ ይደነግጋል፡፡ በዛ መሰረት የሕግ ክፍል የአቤቱታ አጣሪ አባል እንዲሆኑ በመመሪያው ቢቀመጥም፤ ሳይሆን መቅረቱ በድክመት ታይቷል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከመፍትሄ አንጻር፤ ተቋማት ስለአዋጁ ግንዛቤ እንደተፈጠረላቸው በርካታ ማሳያዎች ቢኖሩም፤ ወጥነት ባለው መልኩ ተቋማትን የማሰልጠን እና የማነቃቃት ሥራ አሁንም ሊሰራ ይገባል፡፡ በተቋማቱ ያሉ የቅሬታ ማስተናገጃ ክፍሎች በተገቢው የሰው ኃይል እንዲሟሉ መደረግ ይኖርበታል ሲሉ ያስረዳሉ።

ዳይሬክተሯ እደሚገልጹት፤ አዋጁ ያስቀመጣቸው ግዴታዎች እና ድንጋጌዎች በተገቢው መልኩ እንዲተገበሩ የበላይ አመራሩ በቂ ትኩረት በመስጠት የክትትል ስርዓቶችን የመዘርጋት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡ በታዩ ክፍተቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ተቋማት ኃላፊነት ሊወስዱ ይገባል፡፡

ቅደመ ስነስርዓት ሳይፈጸሙ እና ከስልጣን ውጭ የወጡ መመሪያዎችን ዜጎች በፍርድቤት ሄደው እንዲሟገቱ ለማድረግ የሚቻለው ዜጎች ስለዚህ ሕግ ግንዛቤ ሲኖራቸው ስለሆነ፤ ለዜጎች ግንዛቤ መስጠት ይገባል ሲሉም ያሳስባሉ፡፡

# ሴቶች በሥራ ፈጠራ

**አመለወርቅ ከበደ**



ወ/ት በእምነት ግርማ፣

በትልቅ ጠረጴዛ ዙሪያ እየዞረች ፈጠን ፈጠን በማለት ሻማዎቹን በሥርዓት ሰድራ ለማስቀመጥ ትጣደፋለች፡፡ ቅልጥፍናዋ ልክ እንደምታመርታቸው ሻማዎች ደማቅና እንዲቀርቧት የሚጋብዝ ነው፡፡ ከ ወ/ ት ናድያ ሰይድ ጋር የተገናኘነው ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ባዘጋጀው የሥራ ፈጠራ ኤግዚቢሽን ላይ ምርቶቿን ይዛ በቀረበችበት ወቅት ነው፡፡

የሰንላይት ሻማ አምራች ድርጅት መስራችና ስራ አስኪያጅ የሆነችው ናዲያ ከሰባት ዓመት የአረብ ሀገር ቆይታ ተመልሳ ነው ከሁለት ጓደኞቿ ጋር ወደዚህ ሥራ የገባችው፡፡ አሁን ላይ በተለያዩ ቦታዎች ቅርንጫፍ በመክፈት ከተለመደው ሻማ አንስቶ የተለያየ ሽታ፣ ቅርጽና ቀለም ያላቸውን ሻማዎች አምርተው በመሸጥ ላይ ናቸው፡፡

ናድያ በፀሀፊነት ሙያ ተምራ ብትመረቅም፤ በተማረችው ሙያ ዘርፍ ተቀጥራ እንጀራ ሳትበላበት በ1997 ዓ.ም ወደ አረብ ሀገር የተሰደደችው፡፡ ከሰባት ዓመት የአረብ ሀገር ቆይታ በኋላ በአባቷ መታመም ምክንያት ወደ ሀገሯ መምጣት ግድ ሆነባት እና ተመለሰች፡፡

ከስደት መልስ በተመረቀችው ሙያ በአንድ አስጎብኚ ድርጅት በመዝገብ ቤት እና ጉዳይ አስፈጻሚነት ተቀጥራ መስራት ጀመረች፡፡ በሥራዋ አማካኝነት አሁን አብራት ከምትሰራው ጓደኛዋ ጋር ተዋውቀው ነው ሻማ ወደ ማምረት ሥራ የገቡት፡፡

"በአስጎብኚ ድርጅቱ ከተቀጠርኩ በኋላ አዳዲስ ሰዎችን ለመተዋወቅ እድሉን አገኘሁ። አሁን ከእኔ ጋር በሽርክና የምትሰራው ጓደኛዬ ባጋጣሚ ለምን የራሳችንን የግል ሥራ አንሰራም የሚል ጥያቄ አቀረበችልኝ፡፡ በምን ዘርፍ ልንሰራ እንችላለን የሚለውን እያሰብን እያለ ነበር በሻማ ሥራ ስልጠና የሚሰጥ ድርጅት ሜክሲኮ አየንና ከፍለን ሰለጠን፤ ከዛም ወደ ሥራው ገባን፡፡" ትላለች፡፡

ስልጠናውን ካጠናቀቅን በኋላ ናዲያ ከአረብ አገር ሰርታ የተወሰነ ገንዘብ ስለነበራት ጓደኛዋን ደግሞ ቤተሰብ ረድቷት የሻማ መስሪያ ማሽን ገዙና ቤት ተከራይተው ወደ ስራው ገቡ። ምርት ማምረቱንም አንድ ብለው ጀመሩ፡፡ በወቅቱ ሲያመርቱ የነበረው የተለመደውን የሻማ አይነት ብቻ ቢሆንም፤ ቀስ በቀስ የምርት አይነታቸውን ለማስፋፋት ቻሉ፡፡

"ስንጀምር በተለምዶ እቤት ውስጥ የሚበሩ ሻማዎችን ነበር የምናመርተው፡፡ ሻማዎቹን የምናሽግበት ካርቶን እንኳን ስላልነበረ ስምንት ፍሬ በፌስታል እያሰርን መርካቶ እየወሰድን እናስረክብ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ እየሰራንም ለምንድነው ተደራጅታችሁ የመስሪያ ቦታ የማትወስዱት የሚል ሀሳብ ሰዎች አቀረቡልን፡፡" ስትል ትገልጻለች፡፡

በተሰጣቸው ምክር መሰረት ወደ ወረዳ ቀርበው ቦታ እንዲሰጣቸው የጠየቋቸው የወረዳ ሰዎችም መጥተው የሚሰሩትን ሥራ ከተመለከቱ በኋላ መስሪያ ቦታ ተሰጣቸውና ሥራቸውን አስፋፍተው መስራት ጀመሩ፡፡ ከዛ በኋላ ማሸጊያ ካርቶን በማዘጋጀት ሻማዎችን በካርቶን አሽገው ወደ መሸጥ ገቡ፡፡

ወደ ሻማ ማምረት ሥራ በሚገቡበት ወቅት መነሻ ካፒታላቸው 50 ሺህ ብር እንደነበር ትናገራለች። አሁን ላይ ከሶስት መቶ ሺህ ብር በላይ ካፒታል መድረስ ችለዋል፡፡

ከዚህ በፊት ሻማዎችን በተለያየ ቅርጽ፣ ቀለም እና ሽታ አምርቶ መሸጥ በሀገራችን ስላልተለመደ ቅርጽ ማውጫዎቹን በሀገር ውስጥ ማግኘት አስቸጋሪ ነበር፡፡

ሆኖም ናድያ እንግሊዝ ሀገር ያሉ ጓደኞቿ የተለያዩ ቅርጽ ማውጫዎችን ልከውላት ከተለመደው ቅርጽ ውጭ ሻማን ወደ ማምረት ገቡ፡፡

ከዚህ በፊት ቅርጽና ሽታ ያላቸው ሻማዎች በሀገራችን የሚሸጡ ቢሆንም፤ ከውጭ ሀገራት ነበር የሚገቡት፤ አሁን ላይ ግን ሀገር ውስጥ ማምረት ስለተቻለ የማስገባት ሁኔታው የቀነሰበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ቅርጽ ማውጫ እቃዎቹ በሀገር ተመርተው ለገበያ የሚቀርቡ ቢሆንም ትንሽ ጥራት ላይ የሚቀር ነገር አለው ትላለች፡፡

ወደ አረብ ሀገር ተመልሳ ለመሄድ አስባ ዛሬ ነገ ስትል ባጋጣሚ ወደ እዚህ ሥራ የመግባት እድሉን ያገኘችው ናዲያ፤ "አንዳንዴ ነገሮች እንደተፈለገው ስለማይሆኑ እንጂ ለመስራትም ሆነ ለመኖርም እንደ ሀገር የሚሆን የለም፡፡ በዛ ላይ ብንሰደድም በመጨረሻ ተመልሰን መጥተን የምንሰራው ሀገር ላይ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ የራስ ነገር ኖሮ መስራት ከተቻለ ማን እንደሀገር፡፡" ስትል ትናገራለች፡፡

የእነ ናዲያ ድርጅት ከተመሰረተ ስድስት ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን፣ በእነዚህ ዓመታት አንድ አይነት ሻማ ከማምረት ወጥቶ የተለያየ ቅርጽ ያላቸውን ወደ ማምረት ተሸጋግሯል። ሌላው በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ቅርንጫፎችን በመክፈት በጅምላ ለሱቆች ያቀርባሉ። የሥራ ትዕዛዝ በብዛት በሚኖርበት ወቅት ደግሞ በግዜያዊነት አራት ሰራተኞችን ቀጥረው ያሰራሉ።

ምናልባት ውጭ ሀገራት ኖሮ የመጣ፣ ለሽታ ወይም ለተለየ ዝግጅት ካልሆነ ዘመናዊ ሻማዎችን የመጠቀም ባህሉ በጣም ዝቅተኛ ቢሆንም፤ ናዲያ ምርቶቿን ለመሸጥ የተለያዩ መንገዶችን ከመሞከር አልተጠቀጠበችም።

በዚህም ሻማዎቿን ለሱቆች ከማስረከብ በተጨማሪ፤ ኢኮማኮ፣ ኬ ኢትዮጵያ እና ሌሎች ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ባለ ኮከብ ሆቴሎች ላይም የባዛር ዝግጅት ሲኖር ይዛ ትቀርባለች፡፡

አሁን ላይ የተለምዶ ሻማዎችን ወደ ክልሎች ነው የምንልከው። ባለፈው ዓመት ደግሞ በሴት ነጋዴዎች ማህበር አማካኝነት ምርቶቿን ታንዛኒያ ወስዳ ማስተዋወቋን ትናገራለች። በቀጣይ ሕልሟ በስፋት አምርቶ ለአፍሪካ እና ለዓለም ገበያ ምርቶቹን ኤክስፖርት ማድረግ እንደሆነም ትገልጻለች፡፡

"ከጀመርንበት ግዜ አንጻር ሲታይ አሁን ላይ የሻማው ግብአት በጣም ውድ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ የሻማ ምርቶች ላይ የዋጋ ጭማሪ እንዲኖር ያስገድዳል። ለዚህ መፍትሄ መሆን የሚችለው ግብዓቱን በስፋት ማስገባት ቢቻል የሻማውም ዋጋው ይቀንሳል። ለዚህ ደግሞ ቢያንስ እንደ እኔ ሻማ አምራች የሆኑ ድርጅቶች በማህበር ተደራጅተን የሻማ ግብአት በስፋት የምናስገባበት እድል ቢመቻች ሻማን በቅናሽ ለገበያ ለማቅረብ እና ኤክስፖርት ለማድረግ ይረዳል ፡፡" የሚል እምነት አላት ፡፡

ሌላኛዋ በዝግጅቱ ላይ ያገኘናት ሥራ ፈጣሪ ወ/ት በእምነት ግርማ ትባላለች፣ የልብስ ዲዛይነር ስትሆን፤ የሀገር ልብሶችን ቦርሳዎችን እና በአፍሪካ ጨርቅ የተሰሩ ልብሶችን ሰርታ ትሸጣላች። በእምነት ተወልዳ ያደገችው በኦሮሚያ ክልል ሲሆን፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እዛው በትውልድ ቦታዋ ካጠናቀቀች በኋላ ነበር አዲስ አበባ መጥታ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ልትማር የቻለችው፡፡

በእምነት ምንም እንኳ ዲዛይነር ሆናለሁ ብላ አስባበት ባታውቅም ከልጅነቷ ጀምሮ ለሙያው የተለየ ፍቅር እንደነበራት ታስታውሳለች ፡፡ በእቤት ውስጥ የተለያዩ ዳንቴሎች እና የፌስታል ቦርሳዎችን ታላቅ እህቷ እያሳየቻት ትሰራ ነበር፡፡ አዲስ አበባ የመጣችው በሌላ የትምህርት ዘርፍ ለመማር ነበር፤ ነገር ግን ባረፈችበት የመኖሪያ አካባቢዋ በአጋጣሚ የቴክኒክና ሙያ ስለነበር በጋርመንት ለመማር ወሰነች፡፡

"ወደ ኮሌጅ የገባሁት በ2009 ዓ.ም ነበር፤ ከዚህ በፊት የእጅ ስራዎችን የመስራት ዝንባሌው ስለነበረኝ ጋርመንት ላይ ለመማር አልከበደኝም። ኮሌጅ እየተማርኩ ባለሁበት ወቅት ቤተሰብ የልብስ ማሽን ስለገዛልኝ፤ አንዳንድ ትእዛዞችን እየተቀበልኩ እቤቴ ውስጥ እሰራ ነበር፡፡ ከተመረኩ በኋላ ደግሞ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ተቀጥሬ ሰርቻያለሁ፡፡" ትላለች፡፡

"ቴክኒክና ሙያ ገብቼ መማሬ በልምድ ከሚገኝ እውቀት በላይ በሙያው ዘርፍ ያሉ አሰራሮችን እንዳውቅ እና ዓለም አቀፍ አሰራሮችን ለመረዳ አስችሎኛል፡፡ ምናልባት ባልማር በልምድ ላውቅ እችላለሁ፡፡ መማሬ ደግሞ የበለጠ አካዳሚካል እውቀት ኖሮኝ እንድሰራ እና በዘርፉ ከዓለም አሰራሮች ጋር እንድግባባ እድል ሰጥቶኛል፡፡" ትላለች፡፡

"ተቀጥሬ መስራቴ የበለጠ ሀገርኛውን ዲዛይን አወጣጥ እንዳውቅ አድርጎኛል ፤ በትምህርት የቻይና ወይም የሌሎች የዓለም ሀገራት ዲዛይንን የማውቀው በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ሊሆን ይችላል ፡፡ ወደ ስራ ስገባ እነዚህን ንድፈ ሀሳቦች ወደ ሀገርኛው መቀየር እንዳለብኝ እና በሀገራችን የሚፈለገው የልብስ አይነት እንድለይ እድል ሰጥቶኛል ፡፡" ስትል ትገልጻለች፡፡

ተመርቃ ከወጣች በኋላ በልብስ ቤቶች፣ የትምህርት ቤትና ሌሎች መለዮዎች በሚሰፉባቸው ቤቶች ተቀጥራ ሰርታለች። አሁን ላይ የራሷን ልብስ ቤት ከፍታ ከልጆች እስከ አዋቂዎች ባህላዊ ልብስ ትሰራላች ፤ በተጨማሪነት ደግሞ የሴቶች ቦርሳ እንዲሁም ለሕጻናት የደብተር መያዣ የጨርቅ ቦርሳዎችን ታዘጋጃለች፡፡

ሥራ ስትጀምር እቤት ውስጥ ነበር ሰርታ የምታስረክበው፡፡ ደንበኞቿ እየሰፉ ሲመጡና ሱቅ የመክፈት አቅሙን ስታገኝ የራሷን ሱቅ ከፍታ መስራት ጀመረች፡፡ በራሷ ሱቅ በግል ከመስራት በተጨማሪ እድሉን ስታገኝ አብረዋት ከተማሩ ጓደኞቿም ጋር በሽርክና ትሰራለች። ሌላው የምትሰራቸውን ልብሶች እና ቦርሳዎች በሱቆቿ ከመሸጥ ባለፈ የተለያዩ ባዛሮች ሲዘጋጁ ይዛ በማቅረብ የማስተዋወቅ እና የመሸጥ ስራ ትሰራለች፡፡

አዳዲስ ፈጠራዎች ለማግኘት ማህበራዊ ሚዲያዎችን እንደ ግብዓት እንደምትጠቀም የምትገልጻው በእምነት፤ ያሉ ችግሮችን በማጥናት ለእነሱ መፍትሄ የሚሆኑ የፈጠራ ሥራዎችን ለመስራት እንደምትሞክር በመግለጽ፤ ነባር ስራዎችን በማየት አዲስ ስራዎችን ትሰራለች፡፡

"የሀገር ውስጥ ምርቶችን በመጠቀም ረገድ ገበያው ጥሩ የሚባል ነው፡፡ በማህበራዊ ሚዲያዎች የምናያቸውን ልብሶች ወደ ሀገር ውስጥ ለማምጣት ትንሽ ዋጋው ወደድ ይላል፡፡ ስለዚህ ደንበኞችን ለመሳብ የማያቸውን የውጭ ሀገር ምርቶች ተክቼ ለመስራት እጥራለሁ። ምክንያቱም እኛ የምንሰራው ድሮ እናቶቻችን በሚጠቀሙበት የክር አይነት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከጥራትም ከዋጋም አንጻር የተሻለ ነው፡፡"ስትል ትገልጻለች፡፡

በሥራዋ የሚያጋጥማትን ተግዳሮት የምታነሳው በእምነት፤ አንዳንዴ ደንበኞች ፈልገው ይሁን ወይም በእራሷ ምርጫ ለመስራት ስትፈልግ የምትፈልገውን የቀለም አይነት ያለማግኘት ችግር አለ፡፡ "በዛ ወቅት ከቻይና የሚመጡ ጨርቆችንም ለመጠቀም እሞክራለሁ። ነገር ግን ጨርቁ የጥራት ችግር የሚኖረው ከሆነ ደንበኞች ቢገዙትም ስለማይቆይላቸው በሌላ አይነት ምርጫ እንዲተኩት አደርጋለው። "ትላለች፡፡

በእራሷ ሰፍታ ከምትሸጣቸው የልብስ አይነቶች በተጨማሪ፤ የደንበኞቿን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የተሰሩ ልብሶችን ጎን ለጎን አምጥታ ትሸጣላች፡፡ ዋና የሚባለው የሥራ ግዜዋ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ባሉ ቀናት ሲሆን፤ አንዳንዴ ወደ መኖሪያ ቤቷ አምጥታ ምሽት ላይ ትሰራለች። በርከት ያሉ ትዕዛዞች በሚመጡበት ወቅት ደግሞ ለጓደኞቿም እንደምታስተላልፍ ትናገራለች፡፡

ለደንበኞች ምቹ ነገር መፍጠር እና ጥራት ያለው ነገር መስራት ከተቻለ ልብሱን ወዶት ሌላ ደንበኛም እንዲመጣ ይጋብዛል፡፡ ስለዚህ ቀጣይ እቅዷ ደንበኞች ሊደሰቱበት የሚችሉባቸውን ምርቶች በመስራት፤ ልብሶቹን በክልሎች በማስተዋወቅ እምርታ ለመላክ እቅድ አላት፡፡

"ሌሎች ችግሮች ያሉ ቢሆንም፤ ስራዎቼን ለማስፋፋት እቅድ ስላለኝ የመስሪያ ቦታ ትብብር ቢደረግ መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም በቀን የቤት ኪራይ ከሚገኘው ገቢ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ አለው፡፡ ምናልባት ከመንግስት በኩል የመስሪያ ቤቶች በቅናሽ የሚመቻቹበት ሁኔታ ቢኖር መልካም ነው፡፡" ትላለች፡፡

የተለያዩ ባዛሮች እየተዘጋጁ እንደሆነ በመግለጽ፤ በቀጣይም እንደዚ አይነት ኤግዚቢሽኖች በስፋት የሚዘጋጁበት ሁኔታ ቢመቻች ምርቶቻችን ለማስተዋወቅ እድል ይፈጥራል በማለት ትናገራለች፡፡

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

**አዲስ ዘመን ትናንት፣ አዲስ ዘመን ዛሬም ነው፡፡ ሰው እንጂ በዕድሜ ዘመን ያስ ትውስታና ትዝታ አያረጅም። ትናንት አዲስ የነበረው ዘመን ዛሬም ሕያው ነው። ከትናንቱ ለዛሬ ትውስታችን እንዲሆነን ሸሁ «1 ሺህ 340 ዓመቴ ነው» ሲሉ ሽንጣቸውን ገትረው በልበ ሙሉነት የተናገሩትን እናስታውስ፡፡ ከእሳቸው ጋር ቆይታ ያደረገው የአዲስ ዘመን ጋዜጠኛም ቢጠይቃቸው፤ «ከአሕመድ ግራኝ ጋር ብዙ ጊዜ እንገናኝ ነበር፣ አፄ ቴዎድሮስንም አውቀዋለሁ» ይላሉ፡፡ በ20 ኪሎ ምስር ላይ 30 ኪሎ አፈር እየጨመረ ስለሚሸጠው ነጋዴም ከተጻፈው እናንብብ። ከማያባራው የአንባቢያን የጥያቄ ውሽንፍር ላይ ከቀመው የጳውሎስ ኞኞ ደብዳቤዎችም ጥቂቶችን እናስታውስ፡፡**

### 1 ሺ340 ዓመቴ ነው የሚሉ ሰው ተገኙ

1 ሺ 340 ዓመት ዕድሜ ያለው ሰው በሕይወት ይኖራል ብለን ባናምንም ወሬው እንዳያመልጠን ከአዲስ አበባ ወደ አባኮራ ሰፈር ሄድን። ከሸሁ ቤት ደረስን። እንግዳ መጣ ሲባሉ ከአጣና አልጋቸው ላይ ተነሱ። የሱሪያቸውን ጥብጣብ ሸምቅቀው ታጠቁ። ጋቢያቸውን አደገደጉ፤ ቁልፍ የበዛበትን ካቦርታቸውን ደረቡ። ደህና የቆመጥ ምርኩዛቸውን ይዘው ወደ ውጭ ወጡ።

ሸሁ በሰፈራቸው የተከበሩ ናቸው። በተናገሩ ቁጥር የሰፈሩ ሴቶች "መጀን ያላህ ተዓምር" ይላሉ። ዙሪያችንን የከበቡን ሕጻናት ሸሁን እንደ አንድ ተዓምር ይመለከቷቸዋል። ሸሁ ዓይናቸውን አውኳቸዋል እንጂ በምንም ያልደከሙ ናቸው። ሲስቁ እንዳየነው የሸሁ የታች ጥርሶች ከመበለዛቸው በስተቀር ገና የሚያገለግሉ ናቸው።

ከሸሁ ጋር ጭውውት ጀመርን። "ትክክል ዘንድሮ 1ሺ 340 ዓመት ሞላኝ" አሉን። ስማቸው ሸህ ሙሳ ኪን ሐጂ መሆኑንና አባታቸው ዓረብ፣ እናታቸው የጅማ ሰው መሆናቸውን ነገሩን። ሸህ የተባለውን ማዕረግ መቼ እንዳገኙት ብንጠይቃቸው ገና በልጅነቴ ስወለድ ነው አሉን።

ሸሁ እንደሚሉትና የሰፈሩ ሰውም አሜን ብሎ እንደተቀበለው የተወለዱት በ 617 ዓ.ም ነው። "በ 1 ሺ 340 ዓመት ዕድሜዬ ኢትዮጵያን የገዟትን ነገሥታትና መሳፍንት አውቃለሁ" አሉን። ስለግራኝ መሐመድስ ያውቃሉ አልናቸው። "አዎን አውቀዋለሁ ፤ ብዙ ጊዜ እንገናኝ ነበር። ቀይ ግምጃ የመሰለ ሰው ነው፤ ፈረሱ የሚበላው የወይራ ግንድ ነበር። አንዴ ጃንጀሮ ከሚባል ሀገር መጣና ገረዱን ትቶ ወደ ከፋ ሄደ። ከጥቁር ወንዝ አጠገብ ቆመና የጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን አየ፤ ከዚያ ከፋ ምን ይከፋ አለና ተመለሰ" አሉን።

አፄ ቴዎድሮስንስ ያውቋቸዋል አልናቸው። "ቴዎድሮስ አንዴ ወደ እኛ መጣና በከፋና በጅማ መሐል አለፈ" አሉን።

የተወለዱ ጊዜ ገንዘብ ነበር ስንላቸው "በጨው እንገበያይ ነበር። እኔ ግን ስወለድ ጀምሮ ጫት እየበላሁ ነው ያደግሁት" አሉን። በእድሜዎ ስንት ሚስት አግብተዋል ብንላቸው "ሁለት ብቻ" አሉ። ሚስቶችዎም እንደርስዎ ባለዕድሜ ነበሩ አልናቸው። አይደሉም አሉን። ሁለት ልጆች ወልደው እንደነበርና ሁለቱም በምኒልክ ጊዜ መሞታቸውን ነገሩን።

ሸሁ ላቀረብንላቸው ጥያቄ ሁሉ የሰጡን መልሶች ትክክል አይደሉም። የሰፈሩ ሰው ግን ሸሁ በእርግጥ 1 ሺ 340 ዓመት ዕድሜ አላቸው ብሎ ያምናል።

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 23 ቀን 1957 ዓ.ም)**

### እህልና አፈር ደባልቀው የሸጡት ተፈረደባቸው

እህሉን ከአፈር ቀላቅሎ የሸጠው ታደሰ ፀጋዬ በተከሰሰበት ወንጀል በ3 ወር እስራት እንዲቀጣ የሞረት ወረዳ ፍ/ቤት ከትናንት በስቲያ በዋለው ችሎት ፈረደ፡፡

ተከሳሹ በሞረት ወረዳ ግዛት ሰኔ 17 ቀን 1964 ዓ.ም በአንጭቆረን በዋለው የቅዳሜ ገበያ ከግማሽ በላይ አፈር የሆነ 50 ኪሎ ክብደት ያለው ምስር ነው በማለት አቶ መንግሥቴ ለተባሉት ሰው በ10 ብር ከሸጠ በኋላ፤ ወደ ሌላ ጀንያ እስኪገለብጥ ድረስ ከሥፍራው ጠፍቶ ነበር፡፡

ከሠላሳ ኪሎ የሚበልጥ አፈር የተቀየጠበትን ምስር የገዙት አቶ መንግሥቴ ባቀረቡት አቤቱታ፤ ተከሳሹ ተፈልጎ ወዲያውኑ ተያዘ፡፡ በዚህም አፈጻጸም፤ ሞረት ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሶ ቀርቦ በሰጠው የእምነት ቃል ድርጊቱን ከማመኑም በላይ በማስረጃ ስለተረጋገጠበት፤ ፍ/ቤቱ በ3 ወር እስራት እንዲቀጣ የፈረደበት መሆኑን ሕግ አስከባሪው የአሥር አለቃ ለገሠ አርጋው ገልጠዋል፡፡

**(አዲስ ዘመን ሰኔ 20 ቀን 1964ዓ.ም)**

### አንድ ጥያቄ አለኝ

**-ይድረስ ለጳውሎስ ኞኞ**

*የሞት መድኃኒት ምንድነው?

**የሻምበል ባሻ አፈራው ምስክር**

-መቀበር ነው፡፡ ከተቀበሩ ወዲያ ሞት መግደል አይችልም፡፡

*ሰኔ 13 ቀን በወጣው ዓምድዎ ስለሰው ሞት ዜና በራዲዮ ሲነገር የሚያስከፍሉት ሰባ ብር ነው ያሉት ሰባ አምስት ብር መሆኑን እንደገና ይግለጡልን፡፡

**ከኢትዮጵያ ሬዲዮ ትራፊክ**

-ከምኔው አደገ? ግሩም አስተዳደግ ነውና ይሸንኑ እወቁላቸው፡፡

*አንዳንድ ወንዶች ለጊዜው ጥሩ ለመምሰል ቅልስልስ ይሉና ጥቂት ቆይተው ይለወጣሉ፡፡ ለምን እንዲህ ይሆናሉ?

**አዜብ ብርሃኔ**

-ድመት ጭራዋን የምታወዛውዘው የምትፈል ገውን ጣፊያ እስኪጥሉላት ድረስ ነው፡፡ አንዳንዱም ወንድ እንዲያ የሚሆነው የሚፈልገውን እስቲያገኝ ድረስ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ጣፊያውን እንዳገኘች ድመት ጠባዩን ይለውጣል፡፡

*ዶሮ በአንድ እግሯ የምትቆመው ስትፀልይ ነው የሚሉት እውነት ነው?

**ስንታየሁ ማንደፍሮ**

-መታረድና ሞት እንደሆን አይቀርላት ለምኑ ነው የምትፀልየው? ጽድቅና ኩነኔ ስለሌለባት መፀለይዋ አይደለም፡፡

**(አዲስ ዘመን ሰኔ 20 ቀን 1964ዓ.ም)**

*ውሻ ሁል ጊዜ በፊት ለፊት በር የማይጮኸው ለምንድነው?

**ዐቢይ ወንድሙ ተፈሪ**

-ጠላት በጓሮ በር ነው የሚያጠቃው እያለ፡፡

**(አዲስ ዘመን ታኅሣሥ 22 ቀን 1957ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## እሥራኤል የአየርላንድ ኤምባሲዋን ልትዘጋ ነው

እሥራኤል የአየርላንድ ኤምባሲዋን "በፀረ-እሥራኤል ፖሊሲ" ምክንያት ልትዘጋ መሆኗን አስታወቀች። እሥራኤል የአየርላንድ መንግሥት ለፍልስጤም የሀገርነት እውቅና መስጠትን ጨምሮ እያራመደ ባለው "ጫፍ የረገጠ ፀረ-እሥራኤል ፖሊሲ" ምክንያት የደብሊን ኤምባሲዋን ልትዘጋ እንደምትችል አስታውቃለች።

ባለፈው ግንቦት ወር አየርላንድ ለፍልስጤም የሀገርነት እውቅና መስጠቷን ተከትሎ እሥራኤል አምባሳደሯን ጠርታለች። ደብሊን ደቡብ አፍሪካ በእሥራኤል ላይ በዓለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት (አይሲሲ) ያቀረበችውን የዘር ማጥፋት ክስ በዚህ ሳምንት በመደገፏ እሥራኤልን የበለጠ አናዷታል።

የእሥራኤል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫ "በደብሊን ያለውን የእሥራኤል ኤምባሲ ለመዝጋት ውሳኔ ላይ የተደረሰው የአየርላንድ መንግሥት እያራመደ ባለው ጫፍ የረገጠ ፀረ-እሥራኤል ፖሊሲዎች ምክንያት ነው። "የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጌዲዮን ሳአር የአየርላንድ መንግሥት እያራመደ ያለው የፀረ-ጽዮናዊነት ተግባራት የአይሁዷን ሀገር ከመናቅ እና ከማንኳሰስ የመነጨ ነው ብለዋል።



የአየርላንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ስምዖን ሀሪስ ውሳኔው የሚያጸጽት መሆኑን እና ሀገራቸው ለሰብዓዊ መብት መከበር እና ለዓለም አቀፍ ሕግ እንደምትቆም ተናግረዋል። "አየርላንድ ፀረ-እሥራኤል ነች የሚለውን ክስ አልቀበልም። አየርላንድ ሠላም ወዳድ፣ የሰብዓዊ መብት እና ዓለም አቀፍ ሕግ አክባሪ ነች" ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኤክስ ገጻቸው አስፍረዋል።

አየርላንድ 'ቱ ስቴት ሶሉሽን' ተግባራዊ እንዲሆን እና እሥራኤል እና ፍልስጤም በሠላም እንዲኖሩ ትፈልጋለች። "የአየርላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚካኤል ማርቲን የሁለቱ ሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንደሚቀጥል እና እሥራኤል ያለውን የአየርላንድ ኤምባሲ የመዝጋት እቅድ እንደሌለ መናገራቸውን አል ዓይን ዘግቧል።

## ምዕራባውያን ሩሲያ ለአጸፋ ጥቃት እንድትነሳሳ እየገፋፏት መሆኑን ፕሬዚዳንት ፑቲን ገለጹ

አሜሪካን ጨምሮ ምዕራባውያን ሩሲያን ከልክ በላይ በመግፋት ለከባድ አጸፋ ጥቃት እንድትነሳሳ እየጎተጎቷት መሆኑን ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን አስታወቁ፡፡ ፕሬዚዳንቱ ከሀገራቸው ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ጋር ባደረጉት ውይይት አሜሪካ እና ምዕራባውያን ለዩክሬን የሚያደርጉት ወታደራዊ ድጋፍ ሩሲያ ለከባድ አጸፋ ጥቃት እንድትዘጋጅ እየገፋፏት ነው ብለዋል፡፡

ምዕራባውያን በሩሲያ ላይ ዘርፈ-ብዙ ጦርነት አውጀዋል፤ ይህም የሩሲያን ቀይ መስመር ያለፈ በመሆኑ ሞስኮ የደኅንነት ስጋት ውስጥ እንድትገባ አድርጓል ነው ያሉት፡፡ በተለይም አሜሪካ ሩሲያን ለማዳከም እና በጦርነቱም እንድትሸነፍ ለዩክሬን ገንዘብን ጨምሮ የጦር መሣሪያ ድጋፍ እያደረገች ነው ማለታቸውን አርቲ ዘግቧል፡፡

አሜሪካ ሩሲያን ለማጥቃት የመካከለኛ ርቀት ሚሳኤሎችን በፖላንድ ድንበር ማስማራቷን ጠቅሰው፤ የሩሲያን የበላይነት ለማዳከምም ቅጥረኛ ወታደሮችን እና የጦር አማካሪዎች መላኳን ገልጸዋል፡፡

ዋሽንግተን ሶቭየት ኅብረትን ለማፍረስ የተጠቀመችበትን ታክቲክ አሁንም እየደገመችው ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ሞስኮ የአሜሪካን እንቅስቃሴ በዝምታ እንደማታልፈው እና ከባድ አጸፋዎችን ልትሰጥ እንደምትችል ጠቁመዋል፡፡



የሩሲያ መከላከያ ሚኒስትር አንደሬይ ቢሎዞቭ አሜሪካ በፖላንድ እና ከሩሲያ በ165 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኙት የጦር ሰፈሮቿ ቶምሃውክ የተሰኙ ክሩዝ ሚሳኤሎችን ልታስወነጭፍ እንደምትችል አመላክተዋል። በተጨማሪም አሜሪካ በስምንት ደቂቃዎች ሞስኮን መምታት የሚችል የመካከለኛ ርቀት ሚሳኤል በጀርመን በኩል ልታስማራ እንደምትችል ገልጸው፤ ለዚህም ሩሲያ በአካባቢው ጠንካራ የአየር መከላከያ ሥርዓት መገንባት እንደሚጠበቅባት መግለጻቸውን ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

በሩሲያ እና ዩክሬን መካከል እየተደረገ ያለው ጦርነት ተባብሶ የቀጠለ ሲሆን ከሰሞኑም ዩክሬን በታጋኖርግ ግዛት ለፈፀመችው የሚሳኤል ጥቃት ሩሲያ በዩክሬን ኢነርጂ መሠረተ-ልማቶች ላይ የአጸፋ ጥቃት መፈፀሟ ይታወሳል፡፡

# ስፖርት





## ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በተለያዩ የጎዳና ላይ ውድድሮች ድል ቀንቷቸዋል

ብርሃን ፈይሳ

በተጠናቀቀው ሳምንት በበርካታ የዓለም ሃገራት በተለያዩ ርቀቶች የጎዳና ላይ ውድድሮች የተከናወኑ ሲሆን፤ ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም በአሸናፊነት ሊያጠናቅቁ ችለዋል፡፡ ከማራቶን ውድድሮች መካከል አንዱ የአቡዳቢ ማራቶን ሲሆን፤ አሸናፊው አትሌት ጫላ ከተማ ለመጀመሪያ ውድድሩን ያሸነፈ ኢትዮጵያዊ አትሌት መሆን ችሏል፡፡

አትሌት ጫላ ብርቱ ፉክክር በተደረገበት ውድድር አብዛኛውን ኪሎ ሜትር ሲመራ ከቆየ በኋላ መጨረሻዎቹ ሜትሮች ላይ በወሰደው የበላይነት አሸናፊ አድርጎታል፡፡ ርቀቱን ለማጠናቀቅ የፈጀበት ሰዓትም 2 ሰዓት ከ06 ደቂቃ ከ16 ሰከንድ ሆኖ ተመዝግቦለታል፡፡ ይህ ሰዓት በግሉ ካስመዘገበው ፈጣን ሰዓት በጥቂት ሰከንዶች ብቻ የዘገየ ቢሆንም በአቡዳቢ ማራቶን ከተመዘገቡት ስድስት ፈጣን ሰዓቶች መካከል አራተኛው ነው፡፡ ውድድሩን በድል መወጣቱን ተከትሎ በስፍራው ለነበሩ መገናኛ ብዙኃን በሰጠው አስተያየትም ‹‹የአየር ሁኔታውም ሆነ ውድድሩ ምርጥ ስለነበር አሸናፊ ልሆን ችያለሁ፡፡ በአቡዳቢ ማራቶን አሸናፊ የሆንኩ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ በመሆኔም ኮርቻለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ጥቂት የማገገሚያ ጊዜ የሚኖረኝ ሲሆን፤ ወደ ልምምድ በመመለስ ሃገሬን የሚያስከብር ውጤት ለማስመዝገብ እሠራለሁ›› ብሏል፡፡

እጅግ ጠንካራ ፉክክር የታየበትና የጎዳና ውድድር እስከማይመስል ድረስ አሸናፊውን አትሌት እስከመጨረሻው ለመለየት አስቸጋሪ በነበረው ውድድር ከአንድ እስከ ሦስት ያለውን ደረጃ ይዘው ያጠናቀቁት



አትሌት ጫላ ከተማ በአቡዳቢ ማራቶን ያሸነፈ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሆኗል፣

አትሌቶች የተለያዩት በሦስት ሰከንዶች ብቻ ነው፡፡ የምሥራቅ አፍሪካውያን አትሌቶች የበላይነት በታየበት ሩጫ አሸናፊውን ጫላ ተከትሎ የገባው ጅቡቲያዊው አትሌት ኢብራሂም ቦኸ 17 ሰከንዶችን ብቻ ነው የዘገየው፡፡፡ ከ14 ሰከንዶች በኋላ ሦስተኛ ደረጃን ይዞ የገባው አትሌት ደግሞ ኬንያዊው አትሌት ዌልፍሬድ ኪገን ነው፡፡

በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ የተሰጠው የሕንዱ ካልካታ የ25 ኪሎ ሜትር ውድድር ከትናንት በስቲያ የተካሄደ ሲሆን፤ በሴቶች በኩል ኢትዮጵያዊቷ አትሌት አሸናፊ ሆናለች፡፡ ዘንድሮ ለ9ኛ ጊዜ የተካሄደው ይህ ውድድር በርቀቱ በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ ያገኘ ቀዳሚው ውድድር ነው፡፡ በቀዝቃዛማው የአየር ሁኔታ ከ20 በላይ ሯጮችን በማሳተፍ ውድድሩ ሲካሄድ የምዕራባዊቷን የሕንድ ከተማ ጎዳናዎች ደምቀው ውለዋል፡፡ ጠንካራውን ፉክክር በድል ያጠናቀቀችው ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ሱቱሜ ከበደ ርቀቱን ለማጠናቀቅ 1 ሰዓት ከ19 ደቂቃ ከ17 ሰከንድ ፈጅቶባታል፡፡

በጎዳና ላይ ሩጫዎች ስኬታማ የሆነችው አትሌት ሱቱሜ በመጠናቀቅ ላይ በሚገኘው የውድድር ዓመት በሂውስተን ግማሽ ማራቶን 1 ሰዓት ከ04 ደቂቃ ከ37 ሰከንድ በመግባት የግሏን ፈጣን ሰዓት ማስመዝገቧ የሚታወቅ ነው፡፡ ከዋና ዋናዎቹ ማራቶኖች መካከል በሚጠቀሰው የቶኪዮ ማራቶን ደግሞ 2 ሰዓት ከ15 ደቂቃ ከ55 ሰከንድ በመሮጥ በርቀቱ ታሪክ ስምንተኛዋ ፈጣን አትሌት መሆን ችላለች፡፡ ጠንካራዋ አትሌት በ25 ኪሎ ሜትር ባለፈው ዓመት የገባችበት ሰዓት ዘንድሮ ርቀቱን ካጠናቀቀችበት በአንድ ደቂቃ የፈጠነም ነበር፡፡ በሕመም ላይ የቆየችው አትሌት ሱቱሜ ውድድሩ ሊካሄድ ቀናት ሲቀሩት ተሳትፎዋን አሳውቃ ለአሸናፊነት መብቃቷ በስፖርት ቤተሰቡ አድናቆት አስገኝቶላታል፡፡

አትሌቷ ከውድድሩ በኋላ በሰጠችው አስተያየትም ‹‹በድጋሚ አሸናፊ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፡፡ የውድድሩን ክብረወሰን ለማሻሻል ፍላጎት ነበረኝ ነገር ግን በጉዞ ምክንያት ተዳክሜ ስለነበር አልተሳካልኝም፡፡ ለአዲሱ የውድድር ዓመት ለምሳተፍበት ማራቶን ዝግጅት በማድረግ ላይ እገኛለሁ›› ብላለች፡፡ ከፍተኛ ፉክክር በታየበት ውድድር ሰከንዶችን ብቻ በመዘግየት ሁለተኛ ደረጃን ይዛ ያጠናቀቀችው ኬንያዊቷ አትሌት ቪዮላ ቼፕጌኖ ናት። ባለፈው ዓመት እዛው ሕንድ ላይ በሚካሄደው የዴልሂ ግማሽ ማራቶን ሦስተኛ መሆን የቻለችው አትሌቷ ርቀቱን ለማጠናቀቅ የፈጀባት 1 ሰዓት ከ19 ደቂቃ ከ44 ሰከንድ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም አትሌቷ ‹‹ሁለተኛ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፤ ጠንካራ አትሌቶች በተሳተፉበት ሩጫ ይህንን ደረጃ ማግኘት ቀላል አይደለም፡፡ ጥሩ ብቃት በማሳየቴ በራሴ ተደስቻለሁ›› ስትልም ተናግራለች፡፡ እአአ በ2022 የዚህ ውድድር አሸናፊዋ ባሕሬናዊት አትሌት ደሲ ጂሳ ደግሞ 1 ሰዓት ከ21 ደቂቃ ከ29 ሰከንድ በማስመዝገብ ሦስተኛ ደረጃን ልትይዝ ችላለች፡፡